# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 189 መጋቢት 9 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



eccs
የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ

Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት




# የዓባይ ግድብ

## የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግንባታ በሰባት ወራት ይጠናቀቃል

## - ድልድዩና ሙሉ ሥራው በቀጣይ ዓመት ያልቃል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ ፕሮጀክት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግንባታው በሰባት ወራት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ የፕሮጀክቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ አስታወቁ። በዓባይ ወንዝ ላይ የሚገነባው ድልድይና የፕሮጀክቱ ሙሉ ሥራ በቀጣይ ዓመት እንደሚጠናቀቅም ጠቁመዋል።

የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ እንዳመለከቱት፤ ቀንና ሌሊት በሚሠሩ ባለሙያዎች አማካኝነት የግድቡ ግንባታ የሲቪል ሥራው 99 በመቶ ተጠናቋል።

ዋናው የግድቡ ክፍል 107 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ


የዓባይ ግድብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

ካስማ
ፈርኒቸር

ካስማ የጥራት አርማ !
Gurd Sholla Centurey Mall 3rd floor
+251913230014 ይደውሉ
Kasmafurniture
Kasma Furniture
Kasma.furniture
kasma furniture
kasmafur.com


# የሀገርን ሁለንተናዊ ሰላምና መረጋጋት

## ለማጽናት የፀሎት፣ የንሰሐና የምስጋና መርሀ-ግብር ተካሄደ

**ልጃለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የሀገር ሁለንተናዊ ሰላምና መረጋጋትን ለማጽናት በጋራ የእግዚአብሔርን ምህረት መለመን ያስፈልጋል ሲሉ የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያን ኅብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻዲቁ አብዶ ተናገሩ፡፡ የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት የፀሎት፣ የንሰሐናና የምስጋና መርሀ-ግብር በትናንትናው እለት በመስቀል አደባባይ ተካሂዷል፡፡

በመርሀ ግብሩ ላይ ፓስተር ጻዲቁ አብዶ እንደገለጹት፤ በምድር ለተደረጉ ጥፋቶች ይቅርታን ለማግኘትና የሀገር ሁለንተናዊ ሰላም እንዲሁም መረጋጋት ለማጽናት በጋራ የእግዚአብሔርን ምህረት መለመን ያስፈልጋል፡፡

የመርሀ-ግብሩ ዋና ዓላማ ከእግዚአብሔር ዘንድ


የሀገርን ሁለንተናዊ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




# ቀጣናዊ ትብብር የሚሻው ሁለንተናዊ ዕድገት

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ትንታኔ**

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተስፋ ብርሃን ያዘሉ ቀጣናዊ ሃሳቦች እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስሩ ከነበረበት አዘቅት የተላቀቀም ይመስላል፡፡ የመሠረተ ልማት ትስስሩም ቢሆን ከእለት እለት መሻሻል እያሳየ እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ታዲያ እነዚህ ጉዳዮች ለቀጣናው ሁለንተናዊ ዕድገት የብርሃን ጮራ ፈንጣቂ ብቻ ሳይሆኑ ለቀጣናው ፖለቲካዊ ተሰሚነት ብርቱ ክንድ መሆናቸውን


ቀጣናዊ ትብብር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



AMG STEEL FACTORY
ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory



# ሕዝባዊ ውይይቶቹ ለዘላቂ ሰላም

## የሚኖራቸው ሚና ምንድነው?

**ፋንታነሽ ክንዴ**

በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶች ዜጎችን ለሕልፈተ ህይወት ብሎም ለአካል ጉዳትና ለመፈናቀል እየዳረገ ነው። ግጭቱ በመሠረተ ልማትና በንብረት ላይ ከሚደርሰው ጉዳት በተጨማሪ ማህበረሰቡ ላይ የሥነልቦናና ማህበራዊ ቀውስ በመፍጠር የተባባሰ ችግርን ይፈጥራል።


ሕዝባዊ ውይይቶቹ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ደስታ ገነሜ (ዶ/ር)

# በክልሉ

## 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን የመማሪያ መጻሕፍት ተሰራጭተዋል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን የመማሪያ መጻሕፍት ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መሰራጨታቸውን የክልሉ ትምህርት ቢሮ ገለጸ፡፡

የትምህርት ቢሮው ምክትል ኃላፊና የመማርና ማስተማር ምዘና ዘርፍ ኃላፊ ደስታ ገነሜ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት ከዘጠነኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን መጻሕፍት ማሰራጨት ተችሏል፡፡

የመጻሕፍት ስርጭቱ ለተማሪዎች በቂ አለመሆኑን ጠቁመው፤ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንድ ለአምስት የመጻሕፍት ስርጭት በማድረግ የመማር ማስተማሩን ለማስቀጠል ተሞክሯል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ለሁለተኛ ደረጃ የተሰራጨው መጻሕፍት ላይ በተከሰተው እጥረት የተነሳ ለተማሪዎች የተዳረሰው በቡድን በመሆኑ በሂደት ሙሉ በሙሉ ተደራሽ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

ሁሉም የትምህርት ዓይነቶች በተወሰነ መልኩም ቢሆን ታትመው ተደራሽ መሆናቸውን የተናገሩት ምክትል ኃላፊው፤ በሌላ በኩል አጋዥ መጻሕፍት በተለያዩ ቤተ-መጻሕፍት መቀመጣቸውን አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጻሕፍትን የማሳተም ሥራ የክልሉ ኃላፊነት መሆኑን ጠቁመው፤ የትምህርት ቢሮ መጻሕፍት ለማሳተም እያከናወነ ካለው ሥራ ጎን ለጎን የባለሀብቶችም ተሳትፎና ድጋፍ ከፍተኛ መሆኑን አንስተዋል።

በአካባቢው ቋንቋ የሚታተሙትን ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያሉ መጻሕፍት ለማሳተም ከኅብረተሰቡ 139 ሚሊዮን ብር እንደተሰበሰበ አስረድተዋል፡፡

ምክትል ኃላፊው እንደተናገሩት፤ ስምንተኛ ክፍሎች የክልል ፈተና የሚወስዱ እንደመሆናቸው፤ ለስምንተኛ እና ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች በቅድሚያ የመማሪያ መጻሕፍት ታትሞ ተሰራጭቷል፡፡

በአካባቢው ቋንቋ የሚታተሙ መጻሕፍቶች ላይ በቋንቋ ሂደቱ ላይ ተወያይቶ መግባባት ላይ ለመድረስ ጊዜ መውሰዱን አስረድተው፤ የመማሪያ መጻሕፍት ተቀይረው አዲስ የሚታተሙበትን ሂደት ማዘግየቱንና የጨረታ ሂደት መጓተት እንዲሁም ከማህበረሰቡ ሀብት የማሰባሰብ ሥራ በፍጥነት አለመጠናቀቁ መጻሕፍቱ በጊዜ እንዳይዳረስ ምክንያት መሆናቸውን አመላክተዋል።

የቤተ-መጻሕፍት አገልግሎቱ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጥሩ ሁኔታ እየተሰራበት ቢሆንም፤ በተደረገ ግምገማ በአንደኛ ደረጃ በተለይ በገጠራማ አካባቢዎች ላይ ክፍተቶች መኖራቸውን አመላክተዋል፡፡

በትምህርት ቢሮ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቂ የቤተ-መጻሕፍት አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው የትኩረት አቅጣጫ ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ዶክተር ደስታ እንደተናገሩት፤ በአጠቃላይ በክልሉ የሚገኙ ተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል የማህበረሰቡንም ድጋፍ በማጣመር በከፍተኛ ትኩረት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

# የሁለተኛ ከተሞች እድገት ፍልሰትን እንዲቀንስና የሥራ እድል እንዲፈጠር አስችሏል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የሁለተኛ ከተሞች እድገት ፍልሰትን መቀነስና ለዜጎች የሥራ እድል እንዲፈጠር ማስቻሉን በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ምሁሩ ዳንኤል ሊሬቦ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ዶክተር ዳንኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት በሁለተኛ ከተሞች ላይ የገነባቸው የኢንዱስተሪ ፓርኮች፣ ማኑፋክቸሪንግና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተለየዩ የሥራ አማራጮች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡

በሁለተኛ ከተሞች ላይ ተጨማሪ ሥራዎችን መሥራት ካልተቻለ ዜጎች ለሥራ ፍለጋና የተሻለ ኑሮን ለመኖር ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንደሚፈልሱ የገለጹት ዶክተር ዳንኤል፤ በዚህም የከተሞች እድገት ላይ ትልቅ ተጽእኖ ያሳድራል ብለዋል፡፡

"የሀገር ብልጽግና የሚወሰነው ከተሞች አካባቢ በሚሰራ ሥራ ነው፡፡ አሁን ላይ እየመጣ ያለውን የከተሞች እድገት በአግባቡ ዘመኑን በሚመጥንና በብቁ አመራሮች መምራት ይጠበቅብናል" ብለዋል፡፡

ከተሞች የልማት፣ የፈጠራና የቴክኖሎጂ እድገት ማሳያ መሆናቸውን ገልጸው፤ ዩኒቨርሲቲው የከተሞችን እድገት ለማፋጠን የሚረዳ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

የከተሞችን እድገት ከከተሞች ልማት ጋር በማቀናጀት ከተሞችን ከሚፈለገው ደረጃ ማድረስ እንደሚገባና በኢትዮጵያ እየታየ ያለውን የሁለተኛ ከተሞች እድገት አስፍቶ መጠቀም እንደሚገባ



ዳንኤል ሲሬቦ (ዶ/ር)

ዳንኤል (ዶ/ር) ጠቁመዋል፡፡

ከተሞች በሥርዓት ካልተመሩ ዜጎች ለሥራ አጥነትና ለማህበራዊ ጫና እንዲሁም ለመሰደድ እንደሚዳረጉ ጠቁመው፤ በሁለተኛ ከተሞች እየታየ ያለው እድገት ፍልሰትን በመቀነስ ለዜጎች የሥራ እድል እንዲፈጠርና ከዛም ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችሏል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ በሁለተኛ ከተማነት የሚጠቀሱ እንደ ሀዋሳ፣ ባህርዳር፣ አዳማ፣ ደብረማርቆስ፣ ደብረብርሃን፣ ወላይታ ሶዶ፣ አርባ ምንጭ፣ ሆሳዕና የመሳሰሉ ከተሞች ላይ መሪ እቅዶችን መሠረት ያደረጉ የልማት ሥራዎች በመሠራታቸው ዜጎች ተጠቃሚነታቸው እያደገ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር ዳንኤል ገለጻ፤ ከተሞች ወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ጉዳዮችን በመተንበይ መሠረተ ልማቶችን በማሟላት ለዜጎች ምቹ ከተማና ባሉበት አካባቢ እንዲሠሩ የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል፡፡

መንግሥት በከተሞች አካባቢ ተጨማሪ የልማት ሥራዎች በመሥራት ወጣቶች የራሳቸውን ሥራ በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ መሥ ራት እንደሚገባም ገልጸዋል፡፡

ከተሞች በሥርዓት ከተመሩ ዜጎች በአግባቡ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ ያሉት ዶክተር ዳንኤል፤ ከተሞችን ለዜጎች መኖሪያነት ምቹ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ በአግባቡ መሥራት ይገባል ብለዋል፡፡

የከተሞች ተቋማዊና የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም ተጨባጭ ውጤት እንዲያመጣ ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ የከተሞች እድገት በሀገር ብልጽግና ላይ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት አመላክተዋል፡፡

እንደ ሀገር ስልጡን ከተሞችን ለማፍራት ሁሉም ባለድርሻ አካላት በትብብር መሥራት እንደሚገባቸውም አመላክተዋል፡፡

# ዩኒቨርሲቲው 40 ሺህ የቡና ችግኞችን ለአርሶ አደሩ ለማከፋፈል እየሠራ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ በአካባቢው ምርታማነትን የሚያሳድጉና የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋም የሚችሉ 40 ሺህ የቡና ችግኞች አዘጋጅቶ ለማከፋፈል እየሠራ መሆኑን አስታወቀ፡፡ ዩኒቨርሲቲው በተጨማሪም በርካታ የማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎቶች እየሰጠ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፋሪስ ደሊል(ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው 40 ሺህ የቡና ችግኞች ለአርሶ አደሩ ለማከፋፈል እየሠራ ሲሆን፤ የቡና ችግኞቹ በመጪው አረንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብር የሚተከሉ ናቸው፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከዚህ በፊትም የተሻሉና በሽታን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን በማባዛት ለአርሶ አደሩ ሲሰራጭ መቆየቱን ያስታወሱት ዶክተር ፋሪስ፤ የዩኒቨርሲቲው ችግኝ ጣቢያ ከ40 ሺህ በላይ የቡና ችግኝ እያፈላ ይገኛል ብለዋል፡፡

ዶክተር ፋሪስ አክለውም፤ አብዛኛው የአካባቢው ማህበረሰብ ኢኮኖሚ የተመሰረተው በግብርናው ላይ በመሆኑ በዚህ ላይ በተለያዩ ዘርፎች ጥናትና ምርምር እያደረገ ነው ያሉ ሲሆን፤ የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማረጋገጥ የግብርና ግብዓቶችን በማቅረብ ለሴቶችና ለአቅመ ደካማ አርሶ አደሮች በነጻ የማሰራጨት ሥራ በተለያየ ጊዜ ተሠርቷል፡፡

በአካባቢው አርሶ አደሩን ምርታማና በሽታን መቋቋም የሚችል አዲስ የቡና ዝርያ የማስተዋወቅ ሥራ ለመሥራት የምርምር ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሆነም ነው የገለጹት፡፡


እንደ ዶክተር ፋሪስ ገለጻ፤ በተለይ እንሰት በአካባቢው በሰፊው ለምግብነት የሚውል በመሆኑ የእንሰት ምርምር ማዕከል በማቋቋም ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በጥናትና ምርምሩ ሥራውም እንሰትን የሚያጠቃው በሽታ ከመከላከል፣በሽታውን የሚቋቋሙ ዝርያዎች በማባዛት እንዲሁም እየጠፉ ያሉ ዝርያዎችን ሙሉ በሙሉ ከጥፋት ለመታደግ መሠራቱን ጠቁመዋል፡፡

በዚህም በአዘገጃጀቱ ይባክን የነበረ ረጅም ጊዜና ጉልበት በዘመናዊ መንገድ በመቀየር አዘገጃጀቱ በአጭር ጊዜና በጥቂት ጉልበት እንዲሆን በማድረጉ ረገድ አበረታች ውጤት እንደተገኘ ዶክተር ፋሪስ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል ዩኒቨርሲቲው በክልሉ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ነው ያሉት ዶክተር ፋሪስ፤ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር ለመምህራንና የትምህርት አመራሮች ስልጠና እንዲሁም ለተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት የሚያገኙበት መንገድ ተመቻችቷል፡፡

በተጨማሪም በጤናው ዘርፍ በዞኑ ሌላ ሪፈራል ሆስፒታል ባለመኖሩ የዩኒቨርሲቲው ሪፈራል ሆስፒታል አምስት ሚሊዮን ለሚጠጉ የአካባቢው ማህበረሰብ ክፍሎች አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነ ዶክተር ፋሪስ አስታውቀዋል፡፡

ዶክተር ፋሪስ አክለውም፤ በሆስፒታሉ የሕክምና አገልግሎት ከመስጠት ጎን ለጎን በአካባቢው ላሉ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች ባለሙያዎች አጫጭር ስልጠናዎች እየሰጠ ይገኛል ያሉ ሲሆን፤ ሆስፒታሉ የተለያዩ የግብዓት እጥረት ያለበት በመሆኑ የሚመለከተው ባለድርሻ አካል ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ አድርገዋል፡፡



ፋሪስ ደሊል(ዶ/ር)

# ፋብሪካው የስኳርን ችግር ይቀርፋል ተብሎ ቢገነባም ምንም ምርት እየሰጠ አይደለም

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- የጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ በሀገሪቱ የሚስተዋለውን የስኳር ምርት አቅርቦት ችግር ይቀርፋል ተብሎ ቢገነባም በዚህ ዓመት ምንም ምርት እንዳልሰጠ ተገለጸ፡፡

የጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አበበ ይሁኔ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ፋብሪካው አዲስ የተቋቋመና ሙሉ አቅሙን በመጠቀም ምርት እና ምርታማነትን ለመጨመር ወደ ሥራ የገባ ቢሆንም እያጋጠሙ ባሉ ችግሮች ምክንያት ስኳር እያመረተ አይደለም፡፡

ከእነዚህም ችግሮች በዋነኝነት ኤሌክትሪክ ኃይል ያገኝበት የነበረው የጎንዝላ ሀይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ መበላሸት ምክንያት የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ችግር መከሰቱ እና የማሽን አቅርቦት ችግሮች መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

በዚህ ዓመትም በ6 ሺህ 33 ሄክታር መሬት ላይ የሸንኮራ አገዳ በማምረት 183 ሺህ ኩንታል የስኳር ምርት ለማግኘት የታቀደ ቢሆንም ባጋጠሙ ተግዳሮቶች ምክንያት እስካሁን ምንም ምርት አለመመረቱን ነው ያስታወቁት፡፡

አቶ አበበ እነዚህ ችግሮች የፋብሪካውን ምርታማነት ከማሳጣት ባለፈ በውስጡ ለሚገኙ ሠራተኞች ደመወዝ ለመክፈል አዳጋች አድርጎታልም ብለዋል፡፡

በመሆኑም ፋብሪካው ያሉበትን ችግሮች ለመቅረፍ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር አቅርቦት እየጠየቁ መሆኑን አቶ አበበ አስታውቀው፤ ያሉበትን የማሽን እና የግብአት እጥረቶችም ለመፍታት ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ ብድር በመጠየቅ በሂደት ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በዚህም የሚሠሩ ብዙ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ያሉ ሲሆን፤ ፋብሪካው ለአካባቢው ኅብረተሰብ የሥራ እድል እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለመፍጠር እንደሚሠራ አስታውቀዋል፡፡

ፋብሪካው በቀን 12 ሺህ ቶን ስኳር የማምረት አቅም ያለው ሲሆን፤ በአምስት ዓመት ውስጥ 24 ሺህ 6 መቶ ሄክታር በላይ መሬት የአገዳ ምርት በማልማት ፋብሪካው ያለውን ሙሉ አቅም ለመጠቀም እንደታቀደም አቶ አበበ ተናግረዋል፡፡

ፋብሪካው አሁን ላይ 1500 ቋሚ እና ከ1600 በላይ ጊዜያዊ ሠራተኞች ያሉት ሲሆን፤ ችግሮቹ ተቀርፈው ሥራ ከጀመረ የሚፈጥረው የሥራ እድል በእጥፍ እንደሚጨምር ገልጸዋል፡፡

“የጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ በሀገሪቱ ከሚገኙ ትልቅና ዘመናዊ ፋብሪካዎች አንዱ ነው፡፡ በመሆኑንም ያሉበት ችግሮች የሚመለከታቸው አካላት በተለይም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር በጋራ ያለውን የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ችግር በመቅረፍ የሚገኘውን ምርታማነት ማሳደግ ይገባል” ብለዋል፡፡

ያሉት ችግሮች ከተፈቱም ፋብሪካው ለአካባቢው ማህበረሰብ ብሎም እንደሀገር የሚያስፈልገውን በቂ የስኳር ምርት ለማቅረብ እንደሚቻልም አቶ አበበ አስታውቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን እንደገለጹት፤ ለስኳር ፋብሪካው የኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ እንቅስቃሴ ተጀምሮ የነበረ ቢሆንም በማከፋፈያ ጣቢያ ላይ በደረሰ የትራንስፎርመር ችግር ምክንያት ኃይል መውሰድ አልጀመረም፡፡

ይህም ኃይል እንዲወስዱ ለማድረግ ከጣና በለስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ በባህር ዳር በኩል ወደ ጃዊ ከሚሄደው መስመር ጋር በማገናኘት የማከፋፈያ ጣቢያ ተሠርቶ ነበር፡፡ ነገር ግን የሙከራ ሥራዎች ሳይጠናቀቅ በማከፋፈያ ጣቢያው ላይ በደረሰ የትራንስፎርመር ችግር ምክንያት እንዲሁም ፋብሪካው አዲስ በመሆኑ ኃይል መጠቀም እንዳልጀመሩ ነው ያብራሩት፡፡

በመሆኑም ለፋብሪካው ሥራ ማስጀመሪያ የሚሆን የኤሌክትሪክ ኃይል ለመስጠት የትራንስፎርመር ግዢውን ለማከናወን እና ተከላ የማድረግ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ከስምንት ወራት በላይ ቢሆንም፤ ትራንስፎርመሩ ግዙፍ በመሆኑ እንዲሁም በአካባቢው የጸጥታ ችግር ምክንያት በዚህ ጊዜ ይጠናቀቃል ለማለት እንደሚያዳግት አስታውቀዋል፡፡

በአካባቢው ላይ የሚገኘው የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያም ፋብሪካውን በተወሰነ መንገድ ለማስጀመሪያ የሚሆን ኃይል ከመስጠትም ባለፈ ከፋብሪካው የሚገኙ ተረፈ ምርት በመጠቀም ፋብሪካው የራሱን ኃይል የሚያመርትበት እንደሚሆንም አቶ ሞገስ አስታውቀዋል፡፡



# የደንዲ ሀይቅን ከተፈጥሮ አደጋ ለመጠበቅ የተፋሰስ ልማት እየተሠራ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

ደንዲ፡- የደንዲ ሀይቅን ከተፈጥሮ አደጋ ለመጠበቅና በዙሪያው የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በትኩረት እየተሠሩ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

136 የምዕራብ ሐረርጌ ሞዴል አርሶ አደሮች በምዕራብ ሸዋ ደንዲ ወረዳ በደንዲ ሀይቅ ዙሪያ በሚገኘው አካባቢ በተፋሰስ ልማት ሥራ ያላቸውን ተሞክሮ አካፍለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ በደንዲ ሀይቅ ተገኝተው የተፋሰስ ልማቱን በጎበኙበት ወቅትእንደገለጹት፤ የደንዲ ሀይቅን ከተፈጥሮ አደጋ ለመጠበቅና በዙሪያው ያሉ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የተፋሰስ ልማት እየተሠራ ነው፡፡

በሀይቁ ዙሪያ ለሚገኘው ቦታ የተለየ ትኩረት በመስጠት የምዕራብ ሐረርጌ አርሶ አደሮች በቦታው ተገኝተው ልምድ እንዲያካፍሉ ተደርጓል ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ የልምድ ልውውጡ ከፍተኛ ውጤት የተገኘበት እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

አቶ ጌቱ አክለውም፤ የአፈር መሸርሸር ለአፈር አሲዳማነት መንስኤና በውሃ አካላት ላይ ጫና ከማሳደር አኳያ የራሱ ድርሻ አለው ያሉ ሲሆን፤ በዚህም ሀይቁን ከተፈጥሮ አደጋዎች ለመጠበቅና በዙሪያው ሰፋፊ ልማቶችን ለማልማት ጠንካራ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ጌቱ ገለጻ፤ በሀይቁ አካባቢ በተሠራው እርከንና የተፋሰስ ሥራ የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬ ይተከላሉ፡፡ የሚተከሉት አትክልቶች የሀይቁን ተፈጥሯዊ ገጽታና የአካባቢውን ሥነ-ምህዳር ከመጠበቅ ጎን ለጎን ለአካባቢው ማህበረሰብ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ መሆን የሚችል ነው፡፡

በተጨማሪም የንብ ማነብ ሥራዎች ይሠራሉ ያሉ ሲሆን፤ ይህም የሀይቁን የቱሪዝም ገቢ ለማሳደግና የቱሪስት የቆይታ ጊዜ ለማራዘም ውጥን የያዘ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በሀይቁ ዳርቻ በሚገኘው አካባቢ አርሶ አደሮች በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የገብስ ሰብል ይዘሩበት እንደነበር ያስታወሱት ቢሮ ኃላፊው፤ አሁን የተያዙ የልማት ፕሮጀክቶችን እውን ማድረግ ከተቻለ አርሶ አደሩን በፊት ከሚያገኘው ገቢ እጥፍ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ጌቱ አክለውም፤ በክልል ደረጃ በ6ሺህ 465 ተፋሰሶች አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኪሎ ሜትር እርከን ለመሥራት ታቅዶ እስካሁን አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ኪሎ ሜትር እርከን ተሠርቷል፡፡

የተፋሰስ ልማት የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ከማሳደጉም በላይ የውሃ ሀብቶች ለመጠበቅ እንዲሁም ከንክኪ ነጻ የሚደረጉ ስፍራዎች የከብቶች ግጦሽ ለማግኘት እንደሚያግዝ አቶ ጌቱ አስታውሰዋል፡፡

የምዕራብ ሸዋ ዞን ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተረፈ አራርሳ በበኩላቸው፤ ደንዲ ሀይቅ በእሳተ ጎሞራ የተፈጠረ በመሆኑ የአካባቢው መልክአ ምድር ለአፈር መሸርሸር ተጋላጭ ነው ያሉ ሲሆን፤ በዚህም ምክንያት አካባቢውን ለማልማትና ሀይቁን ከጥፋት ለመጠበቅ ጠንካራ የተፋሰስ ልማት እየተሠራ ነው፡፡

ከባለፉት ሦስት ዓመታት ጀምሮ የእርከን ሥራው ሲሠራ መቆየቱን ያነሱት አቶ ተረፈ፤ በዘንድሮ ዓመትም የበለጠ ለማጠናከር ከምዕራብ ሐረርጌ ከመጡ አርሶ አደሮች ልምድ ተወስዷል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ተረፈ ገለጻ፤ የተፋሰስ ሥራዎቹ የአካባቢውን የተፈጥሮ ጸጋ ለመጠበቅና የሀይቁን ዳርቻ ለቱሪስት ሳቢ ለማድረግ የሚያግዝ ነው፡፡

# የሴፍቲኔት ፕሮጀክት ባመቻቸልን የሥራ ዕድል በመጠቀም የተሻለ ሕይወት እየመራን ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የሴፍቲኔት ፕሮጀክት ባመቻቸልን የሥራ ዕድል በመጠቀም ከበፊቱ የተሻለ ሕይወት እየመራን ነው ሲሉ የአዲስ አበባ የከተማ ልማታዊ የሴፍቲኔት እና ሥራ ፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ገለጹ።

የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ወይዘሮ ዓለም ወርቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ፕሮጀክቱ የከተማ ግብርናን ተጠቃሚ እንዳደረጋቸው እና በተፈጠረው የሥራ እድል ተጠቅመው የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል መቻላቸውን ተናግረዋል። በዚህም የቤተሰባቸውን የዕለት ጉርስ ከመሸፈን አልፈው በወር ከሚያገኟት መቆጠብ እንደቻሉ ጠቁመዋል።

ከዚህም ባለፈ ተጨማሪ ገቢ በሚያስገኙ የሥራ ዘርፎች መሰማራት እንደሚፈልጉ የገለጹት ወይዘሮ ዓለም፤ ፕሮጀክቱ የእማዎራና የአባዎራዎችን የገቢ አቅም በማሳደግ በዘላቂነት ኑሮአቸውን የሚደጉሙበት መሆኑ እንዳስደሰታቸው ተናግረዋል።

በከተማ የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት ተጠቃሚ በመሆናቸው ኑሮአቸውን በአግባቡ ለመምራት መቻላቸውንም ወይዘሮ ዓለም ተናግረዋል።

ሌላኛው የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ አቶ መንግሥቱ ጸጋው በበኩላቸው፤ ካለፈው ዓመት ጀምሮ በሴፍትኔት ፕሮጀክት ታቅፈው በከተማ ግብርና በመሰማራት ቋሚ ገቢ ከማግኘታቸውም በላይ የተለያዩ ስልጠናዎች ተሰጥቷቸው የሥራና የቁጠባ ባህላቸው እንደተሻሻለ አስረድተዋል።

ፕሮጀክቱ ኑሮአቸውን ለመምራት የሚያስችል የገቢ ምንጭ እንደፈጠረላቸው ጠቅሰው፤ በቀጣይም ያለባቸውን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ አቅደው እየሠሩ መሆኑን ገልጸዋል።

ከሥራ ጎን ለጎን በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በመሰማራት የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል መቻላቸውን የገለጹት አቶ መንግስቱ፤ በተለይ በቆጠቡት ገንዘብ በአዋጭ የሥራ መስክ ላይ በመሰማራት ውጤታማ መሆን እንደሚፈልጉ ተናግረዋል።

ፕሮጀክቱ ልጆቻቸውን ለማስተማር፣ በምግብ ራስን ለመቻል፣ያመረትነውን ምርት ለራሳችን እንድንጠቀም እና ለገበያ እንድናቀርብ አስችሎናል ያሉት ደግሞ ወይዘሮ ትዕግስት ግርማይ ናቸው።



**አቶ መንግስቱ ጸጋው**



**ወይዘሮ ዓለም ወርቁ**



**ወይዘሮ ትግስት ግርማይ**

እንደ ወይዘሮ ትዕግስት ገለጻ፤ ፕሮጀክቱ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች በከተማ ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም በመታቀፋቸው ኑሮአቸውን በአግባቡ እንዲመሩ ከማስቻሉም በላይ ሦስት ልጆቻቸውን ማስተማር እንዳስቻላቸውም ጠቁመዋል።

ሴፍቲኔት የሰው እጅ ከማየት አላቆ ራሳቸውን እንዲችሉ እንዳደረጋቸው ጠቅሰው፤ ሠርተው ራሳቸውን ከመደጎም በተጓዳኝ ለሌሎች አርዓያ መሆናቸው እንዳስደሰታቸው ተናግረዋል።

# ቀጣናዊ ትብብር የሚሻው...

ምሁራን ይናገራሉ፡፡

የኢትዮ-ሶማሌላንድ፣የኢትዮ-ኬንያ፣ የኢትዮ-ታንዛኒያ፣የኢትዮ-ሩዋንዳ ስምምነቶች በቀጣይ ቀጣናዊ ብልጽግና የሚያስገኙ ስለመሆናቸው ትልቅ ግምት ተሰጥቷቸዋል፡፡ በኢትዮ-ኬንያ የመንገድ መሠረተ ልማቶች፣ የላሙ ፕሮጀክት፣ የቤልት ኤንድ ሮድ ኢንሼቲቭ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ የኢትዮ-ጅቡቲ የኢኮኖሚ ትስስርና የውሃ ዝርጋታዎች በቀጣናዊ ትብብሩ የጋራ ተጠቃሚነት ካረጋገጡት መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

በጋራ የማደግን ውጥን ለማሳካት ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉርብትና የሚሻ ነው፡፡ አሁን ላይ ላለው ስር የሰደደ አለመረጋጋትና ድህነት ማስወገድ የሚቻለው ሰጥቶ በመቀበል መርህ ሀብቶችን በጋራ መጠቀም ሲቻል ነው የሚሉ ምሁራን ተበራክተዋል፡፡

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአፍሪካ ጉዳዮች ከፍተኛ ተመራማሪ ግዛቸው አስራት (ዶ/ር) ሀገራቱ ባላቸው ማህበራዊ ትስስር ላይ የመሰረተ ልማትና ሀብቶችን በጋራ የመጠቀም መርህ ማሳደግ ቢችሉ ቀጣናዊ ተጠቃሚነታቸውን በአጭር ጊዜ ለማረጋገጥ ያላቸው እድል ከፍተኛ ነው ይላሉ፡፡

ሀገራቱ ዜጎቻቸውን ከድህነት አረንቋ ለማላቀቅ ያላቸውን ማህበራዊ ግንኙነቶች በማጠናከር ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትስስር ማጎልበት ግድ ይላቸዋል የሚሉት ዶክተር ግዛቸው፤ ጠንካራ የሆኑ ቀጣናዊ ተቋማት መገንባት አስፈላጊ ነው ባይ ናቸው፡፡



ግዛቸው አስራት(ዶ/ር)

የዓባይ ግድብ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ችግሮችን በመፍታት አብሮ የማደግና የመልማት ምሳሌ እንደሆነም ይናገራሉ፡፡

በተጨማሪም በቀጣናው ለሚገኙ ተቋማት መዋጮዎችን በማዋጣትና የሕግ ማዕቀፎችን በመፈተሽ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግና ማጠናከር አስፈላጊ ነውም ይላሉ፡፡ ሀብቶችን በጋራ ከመጠቀም በተጨማሪ ከፍተኛ የእውቀትና የልምድ ሽግግር መፍጠር ተገቢ እንደሆነ ይመክራሉ፡፡

የሚቀረጹት ፕሮጀክቶች ቀጣናዊ አውድ የጠበቀ መሆን እንዳለባቸው የሚገልጹት ዶክተር ግዛቸው፤ ሀገራት በራሳቸው የፖሊሲ መሻሻያዎችን



አረጋ ሹመቴ(ዶ/ር)

በማድረግና ቀጣናዊ ቅኝት በማስያዝ ጭምር መሥራት ይጠበቅባቸዋልም ብለዋል፡፡

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ ሀገራቱ ያሏቸው ሀብቶችን ሰጥቶ በመቀበል መርህ በጋራ የማይጠቀሙ ከሆነ የዜጎች ሥራ አጥነት ቁጥር የመጨመር፣ የአሸባሪዎች መበራከት፣ አለመረጋጋትና ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች መብዛት እንዲሁም ደካማ የሆኑ ተቋማትና መንግሥታት የመፍጠር እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ የማህበረሰብ፣ ሀገራዊና ቀጣናዊ ቀውስ መከሰቱ የማይቀር ነው፡፡

በየሀገሩ ያሉ ውስጣዊ ያለመረጋጋቶች ለቀጣናው መናጋትና በሰጥቶ መቀበል መርህ አብሮ ለማደግ ባለው ሂደት ላይ ከፍተኛ ሰንሰለት ሆኖበታል፤ ይህንን ለመቅረፍም ሀገራት መጀመሪያ ውስጣዊ ችግሮች መፍታት፣ለጋራ አጀንዳ ትኩረት መስጠት፣ፖለቲካዊ ቁርጠኝነትና መተማመን ይጠበቅባቸዋል፡፡

ዓለም ከደረሰበት የሉዓላዊነት ደረጃ አኳያ ወደ ፊት በራሱ አስገዳጅ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ ባይ ናቸው፡፡

ሀገራት የሀብት ልውውጥ በማድረግ ክፍተታቸውን መሙላት ከቻሉ የቀጣናውን ኢኮኖሚ በአጭር ጊዜ ማሳደግ ይችላሉ ያሉት ደግሞ የኢኮኖሚ ባለሙያው አረጋ ሹመቴ (ዶ/ር) ናቸው፡፡ በተጨማሪም ፖለቲካዊ ተሰሚነትን መገንባት የሚቻልበት ነው፡፡

በተለይ የአፍሪካ ቀንድ ኢኮኖሚው እንዳይጎለብት በአሻጥር የተሞላ አካሄድ አለ የሚሉት ዶክተር አረጋ፤ ይንን ማስወገድ ቀዳሚ አጀንዳ መሆን አለበት ይላሉ፡፡

ኢኮኖሚያዊ ትብብር ለማሳደግ ሰላማዊ ግንኙነት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ በሀገራቱ መካከል የብሽሽቅ አካሄድ መቀልበስ እንዳለበት ይመክራሉ፡፡

ትብብሩ በሀገራቱ ላይ አብሮ ማደግ ከቻለ የመሠረተ ልማት ክፍተት ለመሙላት፣ የዋጋ መረጋጋት በቀላሉ ለመፍጠር፣ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ለማሳደግ እንዲሁም ምርትና ማርታማነት እንዲጨምር ያስችላል፡፡

የቀጣናው ሀገራት እርስ በርስ ግንኙነት ከመፍጠር ይልቅ ራቅ ካሉ ሀገራት ጋር ግንኙነት ሲፈጥሩ መስተዋሉ በራሱ በቀጣናው ላይ አሻጥር የተሞላበት አካሄድና የብሽሽቅ ፖለቲካ መንሰራፋቱን የሚያሳይ መሆኑን የሚገልጹት ዶክተር አረጋ፤ የቀጣናው መሪዎች ሚዛናዊ በመሆን ችግሮችን መፍታት እንዳለባቸው ይመክራሉ፡፡

# የዓባይ ግድብ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኮንክሪት ሙሌት እንደሚይዝ የተናገሩት ኢንጂነር ክፍሌ፤ ከዚህ ውስጥ አንድ በመቶው ሥራ ብቻ እንደሚቀር አስረድተዋል።

ኢንጂነር ክፍሌ እንዳስታወቁት፤ የግድቡ የኤሌክትሮ ሜካኒካል በተለይም የተርባይንና ጄኔሬተር ተከላ ሥራው 78 በመቶ ተጠናቋል።

እያንዳንዳቸው 375 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም ያላቸው ሁለት ተርባይን ዩኒቶች በተለያዩ ጊዜያት መገጠማቸውን ያስታወሱት የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ፤ ቀሪ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ተርባይኖች በቀጣይ ወራት ተራ በተራ እየገቡ ይገጠማሉ ብለዋል።

በበርካታ ፈተናዎችና ጫናዎች ሳይበገር ግንባታው የቀጠለው የግድብ ግንባታ በአጭር ጊዜ ውስጥ የኤሌክትሪክ ማመንጫዎቹን ተርባይኖች ሥራ ለማጠናቀቅ ጥረት እየተደረገ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

የግድብ የውሃ ማስተላለፊያ አሸንዳዎች ግንባታ ከ85 በመቶ በላይ መድረሱን ኢንጂነር ክፍሌ አመላክተው፤ በአጠቃላይ ፕሮጀክቱ 95 በመቶ መድረሱን አስታውቀዋል።

የግድብ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግንባታ በሰባት ወራት ውስጥ የሚጠናቀቅ ቢሆንም፤ በዓባይ ወንዝ ላይ የሚገነባው ድልድይና ሙሉ የፕሮጀክቱ ሥራው በቀጣይ ዓመት ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃል ሲሉ ተናግረዋል።

አጠቃላይ ሥራዎችንም በ2017 ዓ.ም በማጠናቀቅ የመላው ኢትዮጵያውያን ኩራት የሆነውን የዓባይ ግድብ ከፍጻሜው ለማድረስ አስፈላጊው ርብርብ እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

የፕሮጀክቱ ግንባታ የኢትዮጵያ ተቋማት የጥራት ተሸላሚ መሆኑ በግንባታው ሂደት ለሚኖረው የሠራተኞቹ ተሳትፎና አጠቃላይ በግድቡ ግንባታ ድጋፍ ለሚያደርጉ አካላት በሙሉ ተጨማሪ የሞራል አቅምን የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለዓባይ ግድብ አስተዋፅኦዎችን በቀላሉ ማበርከት የሚያስችል www.mygerd.com የተሰኘ ድረ ገጽ ይፋ ማድረጉ የሚታወስ ነው።

የግድብ ግንባታ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም የመሰረት ድንጋይ ተጥሎ እንደተጀመረ የሚታወስ ሲሆን፤ የግንባታው 13ኛ ዓመት ከሁለት ሳምንት በኋላ በደማቅ ሥነ-ሥርዓቶች እንደሚከበር ይጠበቃል።

# ሕዝባዊ ውይይቶቹ ለዘላቂ ሰላም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መንግሥት መሰል ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ያለውን ዝግጁነት በመግለጽ፣ ጥያቄ አለኝ ከሚል የትኛውም አካል ጋር ለመወያየት ዝግጁ መሆኑን በተደጋጋሚ ማሳወቁ ይታወሳል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድም (ዶ/ር) ዘላቂ ሰላም ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ተከታታይ ውይይቶችን እያደረጉ ነው፡፡ ውይይቶቹ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከየአካባቢው ከተውጣጡ የሀገር ሽማግሌዎችና ወጣቶችን ያካተቱ ናቸው።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ሕዝባዊ ውይይቶቹ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን የሚኖራቸው ሚና ምንድነው? በቀጣይነትስ ምን ዓይነት ጉዳዮች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል? በሚሉ ጉዳዮች ላይ የባለሙያዎችን ሃሳብ ተቀብሏል።

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ የሰላም ምንጩ ኃይል ሳይሆን ችግርን በውይይትና ምክክር መፍታት ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር እያደረጉት ያለው ሕዝባዊ ውይይትና በበዓላትም የሚያስተላልፉት መልእክት ሰላምን ለማምጣት ትልቅ ሚና የሚጫወት ነው፡፡

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለፈ ከክልል ጀምሮ በተዋረድ ሕዝባዊ ውይይቶችን ማጠናከርና ሕዝቡን ማዳመጥ፣ መሬት ላይ ያለውን እውነትም ለሕዝቡ ማሳወቅ ከተቻለ ብዙ ውጤት ማምጣት ይቻላል ይላሉ፡፡

ዶክተር ሙሉጌታ እንደሚያመላክቱት፤ ኅብረ-ብሔራዊነትን ማጠናከርና ከነጠላ ትርክት ወጥቶ የጋራ ትርክት መገንባት አስፈላጊ መሆኑን የሚያመላክቱት ምሁሩ፤ ሥራ አጥነትና ሌሎችም ሀገራዊ ችግሮች ለግጭት መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡

በመሆኑም በየአካባቢው ከሚስተዋሉ ችግሮች መውጫ መንገዶችን መወያየትና መነጋገር መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባ አጽንኦት ይሰጣሉ።

በአንድ ጉዳይ ላይ የራሳችንን ችግር መመልከት ብቻ ሳይሆን ሌሎች በጉዳዩ ላይ ያላቸው አረዳድና ፍላጎት ምንድን ነው ብሎ መረዳት ይገባል የሚሉት ዶክተር ሙሉጌታ፤ ሌሎችን ማዳመጥና መረዳት ስንጀምር ችግሮችን በኃይል ከመፍታት ይልቅ በምክክር ወደ መግባባት የምንደርስበትን በር እንከፍታለን ሲሉ ያስረዳሉ።

እንደ ባለሙያው ማብራሪያ፤ ችግርን በአንድ ቀን መፍጠር ይቻላል፡፡ ችግርን ለመፍታት ግን ለዓመታት የሚዘልቅ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያላሰለሰ ጥረት ይጠይቃል፡፡

ስለሆነም በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ ችግሮች ራሳችን የፈጠርናቸው ስለሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ሌላ ችግር መፍጠር ሳይሆን መፍትሔ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

ሰላም ለማምጣት ምሁራንን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው አስታውሰው፤ መደማመጥ፣ መነጋገርና ለውይይት በር በመክፈት፤ የበደለ ክሶ የተበደለ ተክሶ በሀገራችን ሰላምን ማስፈንና ወደፊት መራመድ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ አባልና የቦሮ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የውጭና ዓለም አቀፍ ዘርፍ ኃላፊ መብራቱ አለሙ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ዘላቂ ሰላም በአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ የሚመጣ አለመሆኑንና ሁሉም ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን ሚና ሊወጡ እንደሚገባ ነው ያስገነዘቡት።

ለሰላም መደፍረስ ውስጣዊና ውጫዊ መንስኤዎች መኖራቸውን የሚጠቅሱት ዶክተር መብራቱ፤ በተለይ የኑሮ ውድነት፣ የመልካም አስተዳደር እጦትና የፍትሕ መጓደል ለሰላም መደፍረስ ምንጭ እንደሚሆኑ ይገልጻሉ።

በመሆኑም በሀገሪቱ ለሚስተዋሉ ችግሮች መፍትሄ መስጠትና ልዩ ልዩ ፖለቲካዊ ፍላጎቶችን ሊያስተናግድ የሚችል አካታች የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠር ያስፈልጋል ባይ ናቸው።

ከውስጣዊ ፍላጎቶች ባለፈ ውጫዊ ጣልቃ ገብነትም ለሰላም መደፍረስ ሚና ሊኖረው እንደሚችል የሚናገሩት ፖለቲከኛው፤ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ሥራ በመሥራትና ውስጣዊ አንድነትን በማጠናከር በውስጥ ጉዳዮችን ጣልቃ ገብተው ሰላም ሊነሱን የሚፈልጉ አካላትን ፍላጎት ማክሸፍ ይገባል ይላሉ፡፡

የፖለቲካ ባህላችን ከብሽሽቅ ወጥቶ መደማመጥና መተባበር ላይ ያተኮረ መሆን እንደሚገባው የሚጠቅሱት ዶክተር መብራቱ፤ ጥያቄዬ አልተመለሰም ብሎ ወደ ግጭት ከመግባት ይልቅ ሌሎችን ለማዳመጥና በውይይት መፍትሔ ለማምጣት መሥራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

እንደ ፖለቲከኛው ገለጻ፤ ታሪካዊ አረዳዳችንን ጨምሮ በብዙ ጉዳዮች ላይ መስማማት እየጠፋ ነው፡፡ ለዚህ ሁሉ ችግሮች መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ንግግርና ምክክር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር እያደረጉት ያለው ውይይት ለሰላም መስፈን ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነው፡፡

ይሁን እንጂ ውይይቶቹ የአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ የሚንጸባረቅባቸው እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፤ በቀጣይነትም ውይይቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤትን ጨምሮ ከሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል ይላሉ፡፡

ለሀገር ሰላም መስፈን ለብሔራዊ መግባባት ተስፋ የተጣለበት ሀገራዊ ምክክር የውይይት መድረክ መፍጠርና የመፍትሔ ሃሳቦችን ማቅረብ ይጠበቅበታል ያሉት ፖለቲከኛው፤ በዚህ ሂደት የሚገኙ ሃሳቦችም ሀገራዊ ችግሮችን በመፍታት በኩል ትልቅ ሚና እንደሚኖራቸው ያመላክታሉ።

ለአንድ ሀገር ሰላም መሠረቱ የሕዝብ ተሳትፎ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሕዝቡ ራሱን ከግጭት በማራቅና ተሳታፊዎችን በመምከር ወደ ሰላም በማምጣት ሚናውን መወጣት እንደሚኖርበት ይገልጻሉ።

እንደ ባለሙያዎቹ ማብራሪያ፤ ለዘላቂ ሰላም መስፈን ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ዝግጁ መሆን፣ በራችንንም ለውይይትና ምክክር መክፈት ውጤታማ ያደርጋል። ከዚህ አንጻር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር እያደረጉት ያለው ውይይት ለዘላቂ ሰላም መስፈን ጉልህ ሚና የሚጫወት ነው፡፡ ውይይቱን አካታች ማድረግና እስከታች ማውረድ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ መሥራት ይገባል፡፡

# የሀገርን ሁለንተናዊ ሰላምና መረጋጋት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ይቅርታን ለመለመን ነው ያሉት ፓስተር ጻዲቁ፤ እርስ በርስ ይቅር መባባል ሳይቻል የእግዚአብሔርን ምህረት መጠየቅ አይቻልም ብለዋል፡፡

ፓስተር ጻዲቁ እንደገለጹት፤ ጥላቻና መገፋፋትን ወደ ጎን በመተው አንድነትንና ፍቅርን ማስቀደም በዚህ ዘመን አስፈላጊ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ፕሬዚዳንት ዶክተር ጣሰው ገብሬ በበኩላቸው፣ ልዩነቶች እና አለመግባባቶች በዘላቂነት እንዲፈቱ ወደ ፈጣሪ መጸለይ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ የንስሐ፣ የምልጃ እና የምስጋና መርሀ-ግብሩ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን እንዲሁም ወደ ኋላ የማይመለስ እርቅ እንዲፈጠር የወንጌል አማኞች የሚጸልዩበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አክለውም መርሀ-ግብሩ ምዕመኑ ለሀገሪቱ ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ "ጌታ እንዲረዳው" የሚማልድበት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በመርሀ-ግብሩ ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው፣የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ኃላፊ አለምፀሐይ ጳውሎስ፣ የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያን ኅብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻዲቁ አብዶ ጨምሮ ሌሎች የአብያተ ክርስቲያናት ፓስተሮች፣ የፌዴራል ተቋማት የሥራ ኃላፊዎችና የአዲስ አበባ በርካታ የእምነቱ ተከታዮች ተገኝተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ገበያውን የማረጋጋት ጅምር ውጤቶችን ማጠናከር ይገባል!

ዛሬ ላይ የሚታየው የገበያ አለመረጋጋት እና የዋጋ ንረት የዜጎችን የመሸመት አቅምና በልቶ የማደር ሕልውና እየተፈታተነ ይገኛል፡፡ ይሄ ደግሞ በአንድ በኩል የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም የፈጠረው ስለመሆኑ ይነገራል። በሌላ በኩል፣ በአሰራርና ቁጥጥር ሊመለሱ የሚገባቸው ተግባራት በአግባቡ ባለመሰራታቸው ምክንያት የተፈጠረ ስለመሆኑም ይገለጻል፡፡

ይሄን ችግር ከመፍታት አኳያም በመንግስት በኩል ዘርፈ ብዙ ተግባራት ሲከናወኑ፤ የማሻሻያ እርምጃዎችም ሲወሰዱ ቆይተዋል፡፡ ለዚህም፣ በምርትና አገልግሎቶች ላይ የዋጋ ድጎማ የማድረግ፤ የቀረጥ ነጻ አገልግሎት መፍቀድ እና አቅርቦትን ማሳደግ የመሳሰሉ ርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ በእነዚህም መልካም ውጤት ማየት ተጀምሯል፡፡

ለምሳሌ፣ ገበያውን ለማረጋጋት ከተወሰደው ርምጃ አንዱ፣ ፍራንኮ ቫሉታን ለገቢ ምርቶች በተለይም ለመሰረታዊ ሸቀጦች ማስገቢያ ማዋል የሚያስችል አሰራር መዘርጋቱ ነው፡፡ በዚህም በአንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ወደ 18 ቢሊዮን የሚገመት ገንዘብ መንግስት ከግብር ማግኘት የሚገባውን ገንዘብ የተወ ሲሆን፤ ይሄም የሸቀጦች አቅርቦት እንዲጨምር የራሱን ሚና ተወጥቷል፡፡ አቅርቦት ሲጨምር ደግሞ ቢያንስ በገበያ ላይ ምርቶችን እንደ ልብ ማግኘት እንዲቻል አድርጓል፡፡ ለዚህ ደግሞ ዘይት እና መሰል ምርቶችን መመልከት ይቻላል፡፡

ከዚህ ባሻገር የሀገር ውስጥ አምራች ፋብሪካዎችን በመደጎምና አቅማቸውን በማጠናከር በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ የተሰራው ስራ ገበያውን በማረጋጋት በኩል ጉልህ ሚና ተጫውቷል፡፡ በዘይት፣ በፓስታና ማኮሮኒን በመሳሰሉ የፍጆታ ምርቶች ላይ በዋጋም፣ በምርት አቅርቦትም ረገድ መልካም ውጤት ማየት ተችሏል፡፡

ሌላው የመሰረታዊ ፍጆታ ምርቶችን አቅርቦት ከመጨመር አኳያ፣ የግብርናውን ምርትና ማርታማነት ማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚህም የግብርና ምርቶችን በስፋት ማቅረብ እና ቢያንስ የምርት እጥረት እንዳይኖር ማድረግ ተችሏል፡፡ በዚህም በኪሎ እስከ 80 ብር ሲሸጥ የነበረ ቲማቲም፣ ወደ 15 እና 20 ብር እንዲወርድ፤ እስከ 140 ብር ሲሸጥ የነበረ ሽንኩርት፣ ወደ 70 እና 75 ብር እንዲወርድ ተደርጓል፡፡

እንደ ፍጆታ ምርቶች ሁሉ በገበያው ላይ የተወሰደው ርምጃ የግንባታ ግብዓት ቁሳቁሶች ላይም መሻሻልን አምጥቷል፡፡ በዚህ መልኩ በተለይም ሲሚንቶ እና ብረትን የመሳሰሉ የግንባታ ግብዓቶች ላይ ልጓም አልባ የዋጋ ማሻቀብ ተስተውሎ ነበር፡፡ ይሄንን የዋጋ ንረት ለመከላከልም የተለያዩ ርምጃዎች ተወስደው አወንታዊ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

በዚህ በኩል የዋጋ ተመን ከማስቀመጥ ጀምሮ፣ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ችግር ፈጣሪዎችን ለሕግ የማቅረብ ርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ግን በተለይ የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን ወደ ምርት እንዲገቡና፣ በሙሉ አቅማቸውም ማምረት እንዲችሉ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል፡፡ በዚህም የሲሚንቶ አቅርቦቱን ማሳደግ፤ የግንባታ ግብዓት ቁሳቁሶችንም ዋጋ በገበያው እንዲወሰን በማድረግ እንዲረጋጋ ማድረግ ተችሏል፡፡

በዚህ መልኩ ለታየው የዋጋ መረጋጋት ጅምር ውጤት ተደማሪ አቅም ተደርጎ የሚወሰደው ደግሞ፣ በቅርቡ በብሄራዊ ባንክ የተቀመጠው የማክሮ ኢኮኖሚውን የማረጋጊያ አቅጣጫዎች ወደ ተግባር መግባት ነው፡፡ የበዛ የገበያ ሰንሰለትን መቀነስና የደላሎችን ጣልቃ ገብነት መግታት የሚያስችሉ ርምጃዎችም መወሰዳቸው ሌላው የችግሩ መቃለል ምክንያት ነው፡፡

በዚህ ረገድ፣ አላስፈላጊ አሰራርን በሚፈጥሩ ላይ የድለላ ፈቃድን ባለማደስ ደላሎች የሚፈጥሩትን ገበያን የመረበሽ ተግባርን ለመቀነስ የሚያስችል ርምጃ ተወስዷል፡፡ በሌላ በኩል፣ አምራቹና ሸማቹ ባጠረ የገበያ ሰንሰለት የሚገናኙበት አሰራር ተዘርግቷል፡፡ በዚህም በ160 ቦታዎች የተጀመረው የሰንበት ገበያ አሁን ላይ በ940 የሰንበት ገበያዎች መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶችን በቅርበትና በቀጥታ ለተጠቃሚ እየቀረቡ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጂ በዚህ መልኩ የተወሰዱ ርምጃዎች እና ጅምር ውጤቶች በሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሰዋል ተብሎ አፍን ሞልቶ የሚያናግሩ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም በአንድ በኩል፣ ዋጋቸው ቀነሰ የሚባሉ ሸቀጦች የቀነሰው ዋጋቸው አሁንም ቀድሞ ከነበረበት አኳያ ሲታይ ከፍ ብሎ ያለ ነውና፡፡

ለዚህ ሽንኩርትን ማየት ቢቻል፣ 20 እና 25 ብር ሲሸጥ የነበረው ነው 140 ብር የደረሰው፡፡ እናም አሁን ላይ ወደ 70 እና 75 ብር ወረደ ቢባልም፣ ቀድሞ ከነበረበት አኳያ ሲታይ አሁንም ዋጋው እንደጨመረ ያለ ነው፡፡ በሌላ በኩል፣ እንደ ጤፍ እና መሰል የግብርና ምርቶች ላይ አሁንም እየታየ ያለው የዋጋ ንረት ከወዲሁ ሊታሰብበትና እርምት ሊደረግበት የሚገባው ነው፡፡

በመሆኑም በአንድ በኩል ገበያውን ለማረጋጋት የተወሰዱ እና ውጤት እያስገኙ ርምጃዎችን ለይቶ የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ተግባሩን አልቆ ማስቀጠል ይገባል፡፡ በሌላ በኩል፣ ርምጃ ተወስዶ ውጤት ከተገኘባቸው አሰራሮች ልምድ በመውሰድ አሁንም ፈተና ሆነው በቀጠሉ ዘርፎች የሚታየውን የገበያ ችግር ለመፍታት መሥራት ይገባል፡፡

ለዚህ ደግሞ ከኅብረተሰቡም፣ የንግዱን ዘርፍ ከሚመራው አካልም፤ ከፀጥታና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም የሚጠበቅ ኃላፊነት መኖሩን ተገንዝቦ በጋራ መስራት ይገባል፡፡ ይሄ የተቀናጀ አሰራር ሲፈጠር ደግሞ ከማሳ እስከ ማዕድ ያለው የግብይት ሂደት የተሳለጠ ይሆናል፤ ሕገወጦች ለክፋት ተግባራቸው የሚሆን ቀዳዳን እንዲያጡ ያደርጋል፤ ሸማችና አምራቹ በልኩ ተጠቃሚ የሚሆንበትንም እድል ይሰጣል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የግድቡ ስኬት - ለባህር በሩ ብርታት

**ወጋሶ**

ለዘመናት በእቅድ የተያዘ፣ ከመወለዱ በፊት ማሳደጊያ የሚሆን በጀት የተጠየቀበትና የተነፈገ፤ በመጨረሻም በደፋር ውሳኔ፤ በምጥ የተወለደ እና በገዳዮቹ ፊት በሁለት እግሩ ለመቆም የበቃ ነው፡፡ ውልደቱ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ይሁን እንጂ ጥቂት፤ ለማይባሉ አስርት ዓመታት ሲታሰብበት የቆየ ግዙፉ የኢትዮጵያም የአፍሪካም ልጅ ነው፤ ዛሬ የ13 ዓመት እድሜ ሲኖረው፣ ለጠላቱ የምን ጊዜም ስጋትና ብስጭት፤ ለናፋቂዎቹ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ብርሃን መሆን የጀመረ ነው - የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ/የአባይ ግድብ፡፡

ይህ የውዝግብ ምንጭ የሆነው ግዙፍ ግድብ፣ ለኢትዮጵያውያኑ የጥንካሬ ማሳያ እና ማስተሳሰሪያ ገመድ ሲሆን፣ እንደ እነ ግብጽ ላሉ ለሌሎቹ አውርቶ አደሮች ደግሞ የእንጀራ ገመድ በጣሽ ነው፤ (እንዲህ ሲባል የዓባይን ወንዝ ለራስ ብቻ የተሰጠ ስጦታ አድርገው ዋሽተውና ወሽከተው ለዜጎቻቸው ለሚሰብኩ ለማለት እንጂ የተፈጥሮ ሀብቱን በጋራ ለመጠቀም ጥሩ ልብ ያላቸውን ለማለት እንዳልሆነ ልብ ይሏል፡፡)

የወንዙ መነሻ ራሷ ኢትዮጵያ ሆና ሳለች በአጉል ተረት ተረት አይነት ጨዋታ አንዳች አይነት ንክኪ እንዳይኖራት ለዘመናት ስትከለከል ቆይታለች፡፡ ይሁንና አይኑን አፍጥጦ ለመጣው ተጽዕኖ ፈጣሪ አግባብነት ያለው ምላሽ በመስጠት የማይታሙት ኢትዮጵያውያን፤ በምጥ ለተወለደው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ዙሪያ በመረባረብ የተጽዕኖ ፈጣሪ ነኝ ባዩን እቅድና ዓላማ ማከኮላሸት ችለዋል፡፡

ዛሬ እነዚያ ሁሉ ፈተናዎች እና ጫናዎች ታልፈዋል፡፡ በእያንዳንዱ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ የግንባታ ሒደት የተለያዩ ማሰናከያ ድንጋዮች እንዲቀመጡ ቢደረጉም፤ እንዲያደናቅፍ ያስቀመጡትን ድንጋይ ሁሉ ለግንባታው ግብዓት በማድረግ በብልሃትና በጥበብ እዚህ መድረስ ተችሏል፡፡ ይባስ ብሎም ከሳሾቻችን እያዩ የሕዳሴ ግድባችን ብርሃን አብርቶልናል፡፡

ይህን የብርሃን ጭላንጭል ማየት የተቻለው ግን በብዙ ክስና ትንኮሳ ከመሆኑም በላይ፤ በጠላቶቻችን በሚዘረጋብን ሴራ ምክንያት በብዙ የውስጥ ፈተናዎች ውስጥ ሆነን መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ እንዲያም ሆነ ግን ብልሆቹ የኢትዮጵያ ልጆች እርስ በእርስ እንድንባላ የተዘረጋውን ወጥመድ በጥበብ በመበጣጠስ ዛሬ ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

መጋቢት 24 ቀን 2016 ዓ.ም የ13ኛ ዓመት ልደቱን የሚያከብረው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ታዲያ፤ በአህጉር እና ዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ በመሆኑ የስኬትና የእውቅና ሽልማት ተሸላሚ መሆን ችሏል፡፡ ይሄም የዘንድሮ ልደቱን ልዩ ያደርገዋል፡፡ ይህ የኢትዮጵያውያን ዐይን ማረፊያና የአሸናፊነት ተምሳሌት የሆነው ታላቁ የኢተትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ፣ ጉዳዩ ከቤኒሻንጉል ጉምዝ ጉባ ወረዳ ልዩ መጠሪያ ከሆነው ከሰርባ እስከ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ድረስ ቀርቦ አስተማማኝ ማብራሪያ የተሰጠበት ልዩ ምልክታችን ነው፡፡

ዛሬ ዋና ላነሳው የፈለግኩት ጉዳይ ኢትዮጵያ ከወራት በፊት ከራስ ገዟ ሱማሌ ላንድ ጋር ያደረገችው የባሕር በር የምታገኝበት የመግባቢያ ሰነድ ስምምነትን ተከትሎ እየተናፈሰ ስላለው ጉዳይ ነው። ይህም የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ልክ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብም በጅማሬው አካባቢ እየተነናፈሰ የነበረው ተራ ፕሮፓጋንዳ አይነት ሲሆን፣ በሕዳሴ ግድቡ ላይ በወቅቱ ተራ ፕሮፓጋንዳ ይናፈስ እንጂ ከስኬታማነቱ እንዳላስቀረው ለመጥቀስ ያህል ነው፡፡

ሲሆን ሲሆን፣ በተለይ በምስራቅ አፍሪካና በቀጣናው ያሉ አገራት በኢትዮጵያና በራስ ገዟ ሱማሌ ላንድ መካከል የተደረገው የባሕር በር ማግኛ የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ጠቀሜታው ኢትዮጵያን ብቻ እንዳልሆነ ሊረዱ ይገባቸው ነበር፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ ግን አሁን አሁን እየተቆጠረ ያለው የአንዱ እድገት የሌላው ውድቀት ተደርጎ ነው። የአንዱ ሰላም መሆን የሌላው ቁርቁዝና ይመስል መገፋፋት መብዛቱም እየታየ ነው፡፡

ይሁንና ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ስኬታማ መሆን ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት ለምታደርገው ጉዞ መንገድ ጠራጊ ነው የሚል አተያይ አለኝ፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን ለማድረግ አቅደው ያቃታቸው ነገር የለም፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሉን ነገር በኃይል የሚፈጽሙ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በመጀመሪያ ማግኘት የሚሹት የተገባቸውን እንጂ የሌላውን ንብረት አይደለም፡፡ ስኬታማ የመሆናቸውም ምስጢር እሱ ነው፤ በጋራ ሰርቶ በጋር የመልማት ሕልምና መንገዳቸው፡፡

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የባሕር በር ባለቤት እንደነበረች የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ እሱ ሁሉ ቀርቶ ለብዙ ዓመታት ያለ ባሕር በር ኢኮኖሚዋንም ሆነ ሰላሟን ስትገፋ ቆይታለች፡፡ ከእርሷ በጣም በቅርብ ርቀት መጠቀም የሚያስችላት የባሕር በር እያለ እስከዛሬ ድረስ ላልተገባ ወጪ ተዳርጋ ቆይታለች፡፡ ከችግሯ ለመውጣትም በተቻላት መጠን ሁሉ በጎረቤት አገራት የሚገኙ ወደቦችንም ለማልማት ሞክራለች፡፡ አሁንም የጀመረችው መንገድ ይሄው የሕልውናዋን ጥያቄ ምላሽ የመስጠት ጉዞ ነው፡፡

ይሁን እንጂ አፍንጫዋ ስር ባለው የቀይ ባሕር ላይ፣ ከወዲያኛው ጫፍ ኃያላን ናቸው የተባሉ አገራት መጥተው ስፍራውን ሲቆጣጠሩት ያልተነፈሱ አካላት፤ ታትሬ ዜጎቼን በአግባቡ ማኖር እሻለሁ ብላ ቀና ለማለት የፈለገችን ኢትዮጵያ ከወዲህ ወዲያ ለማዋከብ የሚደረግ ጥረት ተገቢ አይደለም፡፡ ይሄን መሰል የከፋት አካሄድም ልክ ሊኖረው፤ የኢትዮጵያን የሕልውና ጥያቄ ምላሽ ማግኘት እንደሚገባውም መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያን እድገትና ለውጥ የማትሻው የግብጽ መንገድ ይታወቃል፤ ኢትዮጵያ በዋጋ የፀናቻት የጎረቤት ሱማሊያ ጉዳይ ግን እውነቱን ካለመረዳት፣ አልያም በግብጽና መሰል ኃይሎች ከመነዳት የሚመነጭ ምክንያቱም፣ ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት ከሶማሊላንድ ጋር ያካሄደችውን ስምምነት አንዴ “አወዛጋቢ ስምምነት ነው፤” ሲሉ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ “ስምምነቱ ጦርነት ከማወጅ የማይተናነስ ነው” ሲሉ ይደመጣሉ። ከዚህ ባሻገር፣ ሲሻቸው ወደ ግብጽ፣ ሲላቸውም ወደተባባሩት መንግሥታት ድርጅት ጉዳዩን ሲያደርሱ ይስተዋላል፡፡

ይሄን መሰል አካሄድ ደግሞ ያኔ በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጅማሮ ላይ ግብጽ ግንባታው እውን እንዳይሆን ስትከተል የነበረውን አካሄድ የሚያስታውስ ነው፡፡ ሆኖም በወቅቱ የግብጽ መቅበዝበዝ የግድቡን እውን መሆን አልገታውም። ምክንያቱም አሸናፊው እውነት ነውና። ለዚህም ነው ግብጽ ብዙ የተዋጋችውና እንዲከስም የጣረችው ፕሮጀክት ዛሬ ላይ ለኢትዮጵያውያን እና ጎረቤቶቻቸው ብርሃንን መሆን የጀመረው፡፡ በዚህም ለወዳጆች ኩራት፣ ለጠላቶች ደግሞ ሃፍረት ሆኖ፤ ከጥፋት መንገዳቸው ተደጋጋሚ ምልልስ ትምህርት የሚወስዱበትን እድል የፈጠረው፡፡

ታዲያ የዓባይ ወንዛችን ስኬታማ መሆን የባሕር በር እንዲኖረን ለምናደርገው ጉዞ አቅም ነው። ከወዲሁ ስኬታማ እንዳንሆን ብዙዎች የተለያየ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ላይ ቢገኙ፤ ትናንትን በትጋትና አልሸነፍ ባይነት ያለፉ ኢትዮጵያውያን ዛሬም ያንን ጽናት እንደሚደግሙት ጥርጥር የለውም፡፡

ዛሬም እንደ ትናንቱ ኢትዮጵያ የማንንም አገር ሉዓላዊነት አትዳፈርም፡፡ ትናንት ከሕዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ ብዙ በሴራ የተጠመዱብንን ወጥመዶች በጥበብ በማለፍ እዚህ መድረስ ችለናል፡፡ እርስ በእርስ ሊያጣሉን በብዙ ዋሽተውብናል፡፡ ልክ የዚያን አይነት ሴራ ዛሬም በየመንገዳችን እንደሚጠብቀን ተረድተንና በሕዳሴ ግድብ ላይ ያደረግነውን ትጋት የባሕር በር ለማግኘት በሚደረገው ሒደትም በመድገም ታሪክ ሰሪዎች እንሁን እላለሁ፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# ፍቅርና ወንድማማችነትን እንድንገልጽበት የተሰጠን የወል የፆም ወር

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሸክታብ)

"ሸገር አዲስ አባ አንቺ ያለሽበት፤
ራጉኤል አይደል ወይ የአንዋር ጎረቤት፤
ቅዳሴና ዛኑን አጥር ቢለያቸው
ፈጣሪ ከሰማይ አንድነት ሰማቸው..

እነዚህን በድምጻዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) የተቀነቀነው ሁለቱን ሀይማኖቶች የመቻቻልና በጉርብትና የመኖር ልዕልና የገለጸበት ሙዚቃ ስንኞች ለዛሬው ጽሁፌ የመግቢያም፣ የሀሳብ ማጠንጠኛም ጉዳይ አድርጌ ተዋስኳቸው። ያገባደድነው ሳምንት በመጀመሪያው እለት (እለተ ሰኞ) ደግሞ ለሀሳቤ መነሻ ምክንያት ሆነኝ። ምክንያቱም እለቱ በክርስትናም (በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች)፣ በእስልምናም እምነት ተከታዮች ዘንድ በጋራ ፆም የጀመሩበት በመሆኑ ነው።

እምነቱ ቅዳሴና አዛኑን በአንድ ያስተሳሰረ፣ በክርስትናው የዐቢይ ፆም፣ በሙስሊሙም የረመዳን ፆም በእኩል ያስጀመረ ቀን ነው። እንዲህ አይነት አጋጣሚ ደግሞ ኢትዮጵያዊነት ደምቀው የሚታዩበት አንድነትና መተሳሰብ ብሎም የሀይማኖቶች መቻቻል የሚንጸባረቅበት ነው። የተለያዩ ብሄሮች ከተለያዩ ሀይማቶች ጋር ተከባብረውና ተቻችለው የሚኖሩባት ሀገራችን ለዓለም የመቻቻል ምሳሌ ሆና የዘለቀችበትን ሕያው ማሳያም ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የፍቅርና የመቻቻል ሀገር ስለመሆኗ በርካታ ማረጋገጫዎችን ማንሳት ይቻላል። ከነዚህ ውስጥ አንዱ የሀይማኖት እኩልነት ይጠቀሳል። የተለያዩ ሀይማኖቶች በፍቅርና በአብሮነት የሚኖሩባት ሀገራችን ለብዙዎች የመልካም አብሮነት ምሳሌ ማሳያ ሆና ቆይታለች።

እነዚህ ሀይማኖቶች ከአምልኮ ባሻገር የሚኖራቸው የእርስ በርስ ቤተሰባዊ መስተጋብር የዜጎችን የመቻቻል መንፈስ የሚመሰክር ነው። ይሄ ደግሞ እንደ ሀገር ለአምልኮም ሆነ ለሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ምቹና አስተማማኝ አካባቢ የመኖሩ ውጤት ነው። ብዝሃነትን ከእኩልነት፣ እኩልነትን ከነጻነትና ከፍትሀዊነት ጋር አጣምራ የያዘች፣ ከማንም በላይ ስለሰብዐዊነት ግድ የሚላት ሀገራችን፤ ብዙዎች ስለሰላምና አብሮነት እንዲመርጧት አድርጓታል።

ይህ የኢትዮጵያዊነት ቀለም መጠሪያ ስማችን እስኪሆን ድረስ በአፍሪካ ነጻነትን፣ በዓለም ደግሞ እኩልነትን ለሰው ልጅ ሁሉ የፈነጠቀ ሆኗል። ሂደቱም ማንም የማይጨቆንበትን፣ ማንም የበላይና የበታች የማይሆንበትን ስርዐት ከመገንባትና ለትውልድ ከማቀበል እኩል ስለብዝሃነት ዋጋ የሚከፍልም ጭምር ነው። በመሆኑም ይህ ሕዝባዊ አንድምታ የሀይማኖት እኩልነትን ፈጥሮ፣ በወንድማማችነት አስተሳስሮና አጋምዶ የመቻቻልና የአብሮነት ደሴት አድርጎናል።

ለዚህ ነጻ ሀሳብ እንደዋነኛ ግብዐት የሚሆነን ሰሞነኛው በክርስትናው የአብይ ፆም፣ በእስልምናውም የታላቁ የረመዳን ጾም መገጣጠም ነው። ይሄ ክስተት ልዩ ትኩረት የሚያሰጠው ከፈጣሪ ሰላምንና አንድነትን፣ ጽድቅንና በረከትን እንድናገኝ በአንድ ድምጽ ስለሀገራችንና ሕዝባችን እንድንጸልይ የጋራ ወር ስለሰጠን ነው።

በአንድ ዓላማ በጾምና ጸሎት ፈጣሪ ፊት መቆም በምንም የማይወዳደር የታላቅ ዋጋ ምንጭ ነው። በተለይ ሀገር በብዙ ችግር እየተፈተነች፤ የተስፋ መንገዷንም እየጠረገች ባለችበት በዚህ ጊዜ፣ ክርስቲያንና ሙስሊሙ ፈጣሪ ፊት ለአንድ ዓላማ መቆሙ ይበል የሚያሰኝ ተስፋ ሰጪ ክስተት ነው። እናም ጊዜው ከፈጣሪ ጋር በጽሞና የምንነጋገርበት፣ በስጋችን ዝለት የነፍሳችንን ዋጋ የምናሰላበት የሕዝበ መምዕኑ የከፍታ ጊዜ ነው።

‹ሀገር ማለት ሰው ነው፣ ሰው ማለት ሀገር› የሚል ጥንተ ብሂል አለ። በዚህ አውድ ሀገር ማለት የሰውነት ነጸብራቅ ነው። ሳር ቅጠሉ፣ ሜዳ አፈሩ፣ አእዋፋት አራዊቱ፣ ወንዝ ጅረቱ፣ አድባር አውጋሩ ያለበት የማንነት ወዝና ጠረን፣ የብዙሀነት ስምና መልክ ነው። ከእርስ በርስ፣ ለእርስ በርስ የምንሰጠውና የምንቀበለው የምናጋራውም፤ ከእኔ ለእናንተ ከእናንተ ለእኔና ከእኛ ለሁላችን የሆነ የታሪክ፣ የባሕል፣ የወግና ልማድ፣ የማንነትና የብዙሀነት ውርርስ ነው።

ሰው ማለትስ? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ ከላይኛው ጋር ተመሳሳይ ነው። ሀገርና ሰው፣ ሰውና ሀገር ተወራራሽ እውነቶች ናቸው። አንዱ ያላንዱ ብቻውን መቆም አይችልም። ሰው ማለት ሀገር ነው ስንል፣ የትኛውን ሰው? የሚለው ጥያቄ ቀድሞ የሚነሳ ነው። ሰው በሚለው የወል መጠሪያ ውስጥ ከተፈጥሮ ውጪ የሆኑ ብዙ ማንነቶች አሉ። ሰው ማለት ሀገር ነው በሚለው ውስጥ የተጠቀሰው ሰው፤ በእምነት፣ በሰብዐዊነት፣ በጨዋነት፣ በወግና ባህል፣ በአብሮነት፣ በመቻቻል፣ በስነምግባር፣ በሕግ፣ በኢትዮጵያዊነት፣ የጸናው ሰው ነው። ይሄ ማንነት ነው ሀገር የሚሆነው።

ኢትዮጵያዊነት ደግሞ ስረ መሰረቱ አብሮነትና መቻቻል ነው። ከሰማኒያ በላይ ብሔር ብሄረሰቦች በጋራ የተሰባሰቡባት፣ የተለያዩ ሀይማኖቶች ተከባብረውና ተቻችለው የሚኖሩባትም ጨዋ ሕዝብና ጨዋ ስርዐት ስላላት ነው። ይሄ ስርዐት ወደፊትም ቀጥሎ ከነበረው የተሻለ ኢትዮጵያዊ መስተጋብርን እንደሚሰጠን አምናለው።

ስርዐት የጨዋነት መነሻ ነው። በዚህ ልክ የመቻቻል ተምሳሌት ሆነን በዓለም ፊት የቆምነው ሰብዐዊነትን ያስቀደመ፣ በአብሮነትና በወንድማማችነት ያጌጠ ስርዐት ስለገነባን ነው። እኚህ እሴቶቻችን በመከባበርና በመቻቻል ብዙ ዘመናትን በአብሮነት እንድንራመድ ያደረጉንም ናቸው። እንደ ሀገር፣ እንደ ሕዝብ፣ በበረታ ሕዝባዊነት ተባብረን የቆምነው ግፍን በሚፈራ፣ ለፍትህ ቅድሚያ በሰጠ ሰብዐዊነት ነው። ‹ወደ ሀበሻ ምድር ሂዱ፣ በዛ ሰውን የማይበድል ራሱም የማይበደል የእውነትና የፍትህ ንጉስ አለ› የሚለው የነብዩ መሀመድ መልዕክት ደግሞ የዚህ ዐቢይ ማሳያ ነው።

እንደተባለውም የወቅቱ ሀገረ ገዢ ንጉስ እንግዶቹን በክብር እና በኢትዮጵያዊ መስተንግዶ እንደተቀበላቸው በርካታ የታሪክ ሰነዶች ይዘክራሉ። ከዚህ ጋር አብሮ የሚነሳ አንድ እውነት አለ። በወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱትን የነብዩ ተከታዮች አሳልፎ እንዲሰጣቸው የተለያዩ የውጪ ሀገራት ለኢትዮጵያ ንጉስ ከእጅ መንሻ ጋር ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም፤ ኢትዮጵያዊው ንጉስ ግን ይሄን አላደረገም። ይሄ ጥንተ ታሪካችን አሁን ላለው ሕዝባዊ መቻቻል፣ ሀይማኖታዊ መከባበር ፈር የቀደደ የታሪክ ምስክራችን ነው።

ጎረቤታሞቹ አንዋር መስጂድ እና ራጉኤል ቤተክርስቲያን ይሄን የአብሮነት መንፈስ ከማጉላት ጎን ለጎን፤ የኢትዮጵያዊነት ቀለም በመሆን ለወንድማማችነታችን የላቀ ማሳያ ሆነው ኖረዋል። ከጥንት እስከዛሬ ሀይማኖታዊ ትስስርን ከማጉላት አኳያ ተምሳሌት በመሆን በዘፈን፣ በስነቃል፣ በተረት ሲወደሱ ኖረዋል። ወደፊትም ይወደሳሉ። የተሳሰርንበት፣ የተጋመድንበት የፍቅርና የአብሮነት ጥንተ ጠዋታችን በእነዚህ በልዩነት ውስጥ ሆነው በተጣመሩ ምልክቶቻችን የሚወከል ነው።

በዚህ የፆም ጊዜን ግጥምጥሞሽ በፈጠረው ቀንና ወርም የእምነቱ አባቶችና ተከታዮች በአዛንና ቅዳሴ፣ ስለሀገርና ሕዝብ ፈጣሪን ሲማጸኑ፣ አቡንና ኡስታዙ፣ ሸክና ቄሱ ስለሰው ልጆች ሲሉ ፈጣሪን ሲለማመኑ፤ የላቀ ፍቅርና አብሮነቱ የሚገለጥበት፤ ተባብሮ መቆሙ የሚጸናበት እንደሚሆንም አምናለሁ።

ይሄ ማንነት ነው ያለልዩነት ተከባብረንና ተቻችለን የመኖርን ታሪክ የሰጠን፤ የፍትሀዊነትና እኩልነት በአንድ ጥላ ስር ሰፍነው በኢትዮጵያ እንዲኖሩ ያደረገው። በቀጣይም የሚያምርብን በልዩነት ውስጥ አብሮ መቆም ነው። ያለስስት፣ ያለአድሎ ሀገር ለመቀየር፣ ትውልድ ለመቅረጽ የምናደርገው ጥረትም ነው አንድ እርምጃ ወደፊት የሚያራምደን።

የሁለቱም እምነቶች የጾም ጊዜአቶች በፍቅር ተጀምረው በፍቅር እንዲጠናቀቁ የሁላችንም ምኞትና ፍላጎት ነው። ቂምና ቅያሜ ጥላቻና መለያየት አይደለም በረመዳን ወቅት፣ አይደለም በአብይ ጾም ወቅት በአዘቦትም የማይፈቀዱ ናቸው። እንድንሰጥ፣ ቸር እንድንሆን፣ እንድንተቃቀፍ፣ በጎ እንድናስብ፣ ጥላቻን በፍቅር፣ ቂምን በይቅርታ እንድንሽር፣ የበደሉንን ይቅር እንድንል እምነቱ ያዛል።

> **ሀገርና ሰው፣ ሰውና ሀገር ተወራራሽ እውነቶች ናቸው። አንዱ ያላንዱ ብቻውን መቆም አይችልም። ሰው ማለት ሀገር ነው ስንል፣ የትኛውን ሰው? የሚለው ጥያቄ ቀድሞ የሚነሳ ነው። ሰው በሚለው የወል መጠሪያ ውስጥ ከተፈጥሮ ውጪ የሆኑ ብዙ ማንነቶች አሉ**

ምክንያቱም የሚያየውን ወንድሙን የማይወድ የማያየውን እግዚአብሄርን ወዳለው ቢል ስህተት እንደሆነ መጽሀፍ ቅዱስ ይነግረናል። በእስልምናውም እንዲሁ ይመስለኛል። እናም ጸሎታችን እንዲሰማ፣ ጾማችን፣ ዱዐችን ዋጋ እንዲያገኝ ከሁሉ በፊት በዙሪያችን ካሉት ጋር መግባባት ይኖርብናል።

በሙስሊሙም ሆነ በክርስቲያኑ ጾምና ጸሎት በፈጣሪ ዘንድ ዋጋ የሚያገኙት በፍቅር ሲጀመሩ፣ በፍቅርም ሲፈጸሙ ነው። ፍቅር የሌለበት ሕገ ስርዐት ለውጤት የማይበቃ መሆኑ እሙን ነው። አላህንም ሆነ እየሱስን በፍቅር ካልሆነ በምንም አንደርስባቸውም። ፍቅር ደግሞ ሌሎችን በማፍቀር፣ ከሌሎች ጋር ተስማምቶና ተዋዶ በመኖር የሚገለጽ ነው። በመተሳሰብና በመከባበር በመተዛዘንም የሚታይ ነው። እንዲህ ባለው የአብሮነት ትስስር፣ እንዲህ ባለው የአብሮነት መተሳሰብና መዋሃድ ካልሆነ ከእስራታችን ነጻ መውጣት አንችልም።

አንዋር መስጂድ እና ራጉኤል ቤተክርስቲያን መርካቶ እንብርት ላይ ሆነው ፍቅርን የሚሰብኩ፣ አብሮነትን የሚናገሩ የወንድማማች ሀውልቶች ናቸው። ለብዙዎቻችን የኢትዮጵያዊነት ምሳሌ ሆነው ዘልቀዋል። ለረመዳንና ለአረፋ ጊዜ ሕዝበ ክርስቲያኑ የወንድሞቹን መስገጃ እያጸዳ፤ በጥምቀትና በፋሲካ ደግሞ ሙስሊም ወንድሞች የክርስቲያኑን ቤተ እምነት አጸድ እያሳመሩ ኢትዮጵያዊነት ምን እንደሆነ በተግባር ሲያሳዩ ኖረዋል። እናም እንዲህ እንደ አሁኑ በጋራ ጾማችን ሰሞን ያለውን የወንድማማችነት መተሳሰብ እውነታ በደመቀና በበረታ መልኩ ማስታወስ ይገባል።

ሁለቱ ታላላቅ ሀይማኖቶች በአንድ ዓላማ ፈጣሪ ፊት ሲቆሙ፣ ሲጾሙና ሲሰግዱ፣ ሲቀድሱና አዛን ሲሉ፣ ሲለማመኑና ዱዐ ሲያደርጉ መመልከትን የመሰለ ታላቅ በረከት የለም። መቻቻልና አብሮነት ከምንም በላይ መንፈሳዊነት የሚንጸባረቅበት እንደመሆኑም፤ ይሄ የጾም ወቅት ከነበረን በላይ እንዲኖረን፣ ካሰብነው በላይ እንዲጨመርልን መንገድ የሚከፍትልን አጋጣሚም ነው። እንደሀገር ካለንበት ችግር ወጥተን በሰላምና በደህንነት እንድንኖር ከፈጣሪ ምህረት የምናገኝበትም ጊዜ ነው።

ጊዜው ከመቼውም በላይ ወደላይ የምናይበት፣ በጾምና ጸሎት ከፈጣሪ ጋር የምንታረቅበት ነው። ምክንያቱም በእርስ በርስ መጨካከን ብዙ ነገሮችን አጉድለናል። በትዕቢት፣ በጥላቻ ፈጣሪን አሳዝነናል። በድፍረት፣ በጭካኔ ያለራሮት ደም አፍሰናል፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ ወንድማማች ሆነን ቆመን እርስ በርስ ተገፋፍተናል። በመሆኑም ይሄ የጾም ወቅት ታሪካችንን የምናድስበት፣ ከፈጣሪ ጋር በመታረቅ ክብራችንን የምንመልስበት ነው። ሙስሊም ከክርስቲያኑ ለአንድ ዓላማ ወደፈጣሪ ሲጸልዩ፣ ስለሀገርና ሕዝብ፣ ስለሰላምና አንድነት፣ ስለደህንነትና በረከት ሲማጸኑ እንደማየት ደስታ የለም። መሻታችንን ተመልክቶ ፈጣሪ እንዲረዳን የሁላችንም ምኞት ነው።

በሀገራችን ብዙ ችግሮች ተከስተዋል። መነሻው ፍቅር ማጣትና ተነጋግሮ አለመግባባት ቢሆንም ከኢትዮጵያዊነት ያፈነገጡ አንዳንድ ማንአለብኝነትም ለዚህ ችግር እንደዋነኛ ምክንያት ይጠቀሳሉ። ሆኖም ተነጋግረን እንዳንግባባ አእምሮና ልባችንን የዘጋነው ከፍቃደ እግዚአብሄር ስለሸሸን ነው። መፍትሄውም ስክነት፣ እርጋታና ጽሞና ናቸው። ስክነት ከራሳችን ጋር እንድንመክር ያደርገናል።

እርጋታ ከፍተቶቻችንን እንድንመለከት፣ ጽሞና ደግሞ ከፈጣሪ ጋር በጸሎት እንድንገናኝ መንገድ ይከፍትልናል። እናም ይሄ ፆማችንን በአብሮነት እንድንጾምና ፈጣሪንም እንድንማጸን የተሰጠን ወር በምክንያት ነውና፤ በዚህ መልኩ ተጉዘን ፍቅር እና ወንድማማችነትን እንድንገልፅበት የተሰጠን መሆኑን በመገንዘብ በዚሁ ልክ ራሳችንን ልንገልጥ ይገባል። እኔም ጾሙ የበረከትና የተስፋ እንዲሆንልን በመመኘት ላብቃል። ሰላም!

# የአውሮፓ ቻምበር - ለኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት እድገት የፖሊሲ ጥናት አንድምታ

**ማህሌት አብዱል**

> **የፖሊሲ ጥናቱ በዋናነት ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ ለሚሰሙ እንደ ግብርና ያሉ የኢንቨስትመንት ሥራዎች መጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በተለይ በለሃብቱ ለኢንቨስትመንት ወደ ኢትዮጵያ ከሚጠይቃቸውና ዋነኛ ግብዓት የሆነው የመሬት አቅርቦት ላይ ያሉ ችግሮችን ለመፈተሽ ይረዳል**

ከሰሞኑ በኢትዮጵያ የሚገኘው የአውሮፓ ቻምበር ለባለሃብቶች ለልማት በሚውል መሬት አቅርቦት ላይ ያተኮረ የፖሊሲ ጥናት ሰነድ ይፋ አድርጓል። 'የመሬት ተደራሽነት፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጪ ላሉ ባለሃብቶች የመሬት አሰጣጥ ሂደትን ማመቻቸት' በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ይኸው ሰነድ፣ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የኢንዱስትሪ ዞኖች ውጪ በልማት ሥራ ውስጥ የተሰማሩ ባለሃብቶች የልማት መሬት ከማግኘት ጋር ተያይዞ እያጋጠሟቸው ያሉ ተግዳሮቶችን አመላክቷል። የፖሊሲ ሰነዱ በአውሮፓ ቻምበር እና በአውሮፓ ሕብረት የገንዘብ ድጋፍ እንዲሁም በጂአይዜድ ትብብር የተዘጋጀ ነው፡፡

ሰነዱ በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች ያሉ የቢሮክራሲ መዘግየቶች፣ ቀድሞ የተዘጋጀ በቂ የኢንቨስትመንት መሬት አለመኖር፣ ከመጠን ያለፈ የካሳ ጥያቄ እና የካሳ አሰጣጥ አስተዳደር ችግሮች (በቀጥታ ለሕብረተሰቡ ከመስጠት ይልቅ ወደ መልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ለማስገባት መወሰኑ) የመሳሰሉ ተግዳሮቶችን አጉልቶ አሳይቷል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በክልላዊ መዋቅርና በመሬት መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች ላይ በየጊዜው የሚደረጉ ለውጦች፣ በልማቱ አካባቢ ለመድረስ የመሰረተ ልማት አውታሮች ውስንነት፣ በፌደራልና በክልል ባለስልጣናት መካከል ያለው የቅንጅት ክፍተት፣ የማጭበርበር ተግባራት፣ የአስተዳደር አቅም ችግሮች እና የሃብት ውስንነቶች፣ የመሬት ድልድል ተመሳሳይ አለመሆን እና የባለሃብቶቹ መሬትን ተገቢ ላልሆነ ተግባር መጠቀም ችግሩን እንደሚያባብሱ በሰነዱ ላይ ተገልጿል፡፡

የፖሊሲ ሰነዱ በኢትዮጵያ መንግስት ሊታሰብባቸው የሚገቡ የውሳኔ ሃሳቦችን አመላክቷል፡፡ ከእነዚህም መካከል ግልፅነትን፣ ፍትሓዊነትን እና ቀልጣፋ የመሬት አስተዳደርን በማስፈን ኢንቨስትመንትን እና የኢኮኖሚ ልማትን የሚያበረታታ ግልፅና ወጥነት ያለው ፖሊሲ መዘርጋት ይጠቀሳሉ፡፡ የመሬት አስተዳደር መሥሪያ ቤቶችን አቅም ማሳደግ፣ የፌደራልና የክልል መንግስት ቅንጅቶችን ማጎልበት፣ የፀረ-ሙስና ርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ እና ግልፅነት ያለው የመሬት መዝገብ ማዘጋጀት ከተነሱት ሌሎች ዋና ዋና ሃሳቦች መካከል ናቸው፡፡

ተጨማሪ ምክረ ሀሳቦች የካሳ ክፍያን ለማስላት መመሪያዎችን ማዘጋጀት እና የመሬት ግምትን እንደ ግብርና ሚኒስቴር ካሉ አካላት ጋር ማስተባበር፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን አገልግሎት ውጤታማነትን ማሻሻል፣ በሁሉም የአስተዳደር እርከኖች የመሬት ምደባ መመሪያዎች ማዘጋጀት፣ ከተፈናቀሉ ግለሰቦች ጋር የምክክር ስብሰባዎችን ማካሄድ፣ በክልላዊ የመሬት አስተዳደር ቢሮዎች የመሬት አሰጣጥ ሂደቶችን ማቀላጠፍ እና እንደ ቬዬትናም ካሉ ሃገሮች የተሳካ የመሬት አስተዳደር ማሻሻያዎች ተሞክሮ ማጥናትን ያካትታሉ፡፡

የፖሊሲ ሰነዱ በኢንተርኔት አማካኝነት የተካሄደ የዳሰሳ ጥናት ሲሆን፣ አንድ ለአንድ የተካሄዱ ቃለመጠይቆች እና ሚኒስቴር መስሪቤቶችን፣ የንግድ ማኅበራትን፣ ባለሃብቶችን እና ምሁራንን ጨምሮ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተካሄዱ የትኩረት ቡድኖች ውጤቶችን ያካተተ ነው፡፡ በተጨማሪም ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሳች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን አዋጅም ቃኝቷል፡፡ የሰነዱ ዓላማ በኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት መሬት ከማግኘት ጋር በተያያዘ የግሉ ሴክተር የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶች በመለየት በግሉ ሴክተር ዕድገት ምቹ ሁኔታ መፍጠር እና የውጭ ኢንቨስትመንትን ወደ ኢትዮጵያ መሳብ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የአውሮፓ ቻምበር ዋና ዳይሬክተር አቶ ባህሩ ተመስገን የፖሊሲውን ይዘት አስመልክቶ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳብራሩት፤ የፖሊሲው ዋና ዓላማ የአውሮፓ ሕብረት በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የውጭ ባለሃብቶች የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመፍታት ነው፡፡ የፖሊሲ ሰነዱ ከዚህ ቀደም የተሰሩ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ የተሰራ ሲሆን በተለይም በግብርና ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ የውጭ ባለሃብቶች ከመሬት አቅርቦት ጋር ተያይዞ እየተፈተኑበት ያሉበትን ሁኔታ በመዳሰስ የመፍትሔ አቅጣጫ የሚያስቀምጥ ነው፡፡

«ለኢንቨስትመንት የግድ መሬት ያስፈልጋል፤ ኢትዮጵያ ደግሞ ሰፊ የመሬት ሃብት አላት፤ ይሁንና ይህንን ሃብት በአግባቡ ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ ሰፊ ክፍተቶች ይታያሉ» ይላሉ፡፡ ይህንን መሬት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ያስችል ዘንድ ምክረ ሃሳብ የሚሰጥ የፖሊሲ ሰነድ መሆኑንም ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ጥናት መነሻነት ሃገር ውስጥ ያሉ የአውሮፓ ሕብረት በተለይ በግብርና ላይ የሚሰሩ ተቋማት ያላቸውን ኢንቨስትመንት የማስፋፋት ፍላጎት እንዳላቸው ያመለክታሉ፡፡

ለዚህ ደግሞ የመሬት አቅርቦት ወሳኝ መሆኑን አቶ ባህሩ አስታውሰው፤ በዚህ ረገድ በ2005 ዓ.ም የወጣው የመሬት አዋጅ በ2007 ዓ.ም በወጣ ማስፈፀሚያ አዋጅ መነሻነት ሥራ ላይ ውሎ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ በኋላም ሌላ አዋጅ ቢወጣም የማስፈፀሚያ ዳይሬክቲቭ ባለመውጣቱ ምክንያት የተለያዩ ችግሮች ሲያጋጥሙ ይስተዋላል፡፡ ማስፈጸሚያ ባወጡትም ክልሎች ላይ ወጥነት ያለው አሰራር ሲከተሉ አይስተዋልም፡፡ ከዚህ አንፃር የፖሊሲ ጥናቱ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን ማስቀመጡን ይናገራሉ፡፡ መንግስትም ከዚህ ጥናት በመነሳት ችግሮቹን እንዲፈታ በማለም የተዘጋጀ ስለመሆኑ ነው ያብራሩት፡፡

በፖሊሲ ጥናቱ የቀረቡ አብዛኞቹ ችግሮች መንግስት የሚያውቃቸው ቢሆኑም ችግሮቹን ለይቶ ወደ መፍትሔ መምጣት ላይ ግን ክፍተት ይስተዋላል ይላሉ፡፡ ይህን ሲያብራሩም «መንግስት ሙስና እንዳለ ያምናል፤ ነገር ግን መሬት ላይ ወርዶ ሙስናን ከስሩ ማድረቅ ላይ ቁርጠኝነት አይታይበትም» ሲሉ ጠቅሰዋል፡፡ የመሬት ባንክ በወረዳ ደረጃ እንደሚቋቋም የተገለፀ ቢሆንም፤ ግን ኢንቨስተሮች ከመጡ በኋላ መሬት ለማቅረብ የመጕራጥ ሁኔታ ይታያል ሲሉ አመልክተው፣ ከዚያ ይልቅ በእያንዳንዱ ወረዳ ያለውን የመሬት ሃብት አስቀድሞ በአግባቡ በመለየት ልክ ሲመጡ መስጠቱ የተሻለ የውጭ ኢንቨስተሮችን የሚስብ እንደሆነ በጥናቱ መቀመጡን ያስረዳሉ፡፡

አቶ ባህሩ እንደሚሉት፤ በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት እንደትልቅ ተግዳሮት ሆኖ የሚቀርበው በመንግስት ተቋማት ውስጥ ያለው ቢሮክራሲ ነው፤ ከፍተኛ መዋለንዋይ ለማፍሰስ የመጣ የውጭ ባለሃብት ረጅምና የተንዛዛ ቢሮክራሲን በትዕግስት ለማለፍ ይገደዳል፡፡ በዚህ ረገድ የአንድ መስኮት አገልግሎት መዘርጋቱ እንደመፍትሔ የሚወሰድ ቢሆንም በሁሉም ደረጃ ያለመስፋቱ ውጤታማነቱን ጥያቄ ውስጥ አስገብቶታል፡፡ በተለይ በአበባ ልማት ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ የውጭ ኩባንያዎች ቢሮክራሲው እየፈጠረ ያለው ችግር ካልተፈታ ባለሀብቶቹ አይናቸውን ወደ ሌላ የአፍሪካ ሃገር ሊያዞሩ የሚችሉበት እድል ሰፊ ነው፡፡

«ለአበባ ልማት የሚያስፈልገው መልካም ምድርና ምቹ የአየር ንብረት መኖሩ ብቻውን በቂ አይደለም፤ ያለው መንግስታዊ አሰራርም ምቹ መሆን ከሌሎች ሃገራት ጋር ተወዳዳሪ የሚያደርጋት በመሆኑ በተቋማቱ ያለውን አሰራር መፈተሽ ይገባል ሲሉ አቶ ባህሩ ያመለክታሉ፡፡ በዚህ ረገድም የፖሊሲ ጥናቱ ያስቀመጣቸው ምክረ ሃሳቦች መኖራቸውንም ነው አክለው ያመለከቱት፡፡ በጥናቱ ላይ በተለይ የግብርና ሚኒስቴርና ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መሳተፋቸውን ገልፀው፤ ከዚህ በኋላ በሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች በመሳተፍ ለትግበራው አወንታዊ ሚና ይጫወታሉ ተብሎ ይጠበቃልም ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ክፍል የመሬት ሕግ ባለሙያ አቶ አበባው አበበ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ሚኒስቴሩ የግብርና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የተለያዩ ሕጎችን በማዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡ በተለይም በቅርቡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ውስጥ በተለይ ኢንቨስተሮቹ መሬት የሚያገኙበትን መንገድ የሚያሻሽል፤ መሬት ካገኙም በኋላ ኢንቨስት አድርገው ሀገሪቱን የሚጠቅም ሥራ እንዲሰሩ የቁጥጥር ስራዎችን ጭምር የሚያስቀምጥ ሕግ ነው፡፡ በዋናነት ደግሞ የባለሃብቶቹን መብት የሚያስከብር ሲሆን፤ መሬት ካገኙ በኋላ መሬቱን የመጠቀም ባለመብትነታቸው እንዲመዘገብ የሚያደርግ ሕግ ነው፡፡ ይህ በቅርቡ ይፀድቃል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን በተለይ አሁን ላይ እየተነሱ ያሉትን ቅሬታዎች ይፈታል የሚል እምነት ተጥሎበታል፡፡

በሌላ በኩል ቀድሞ የፀደቀውና ለሕዝብ ጥቅም ሲፈለግ መሬት ከባለ ይዞታዎች የሚወሰድበት ሕግ መኖሩን አስታውሰው፤ በዚህ ሕግ መሰረት ባለሃብቶች ሲመጡ በቢዝነስ ፕላናቸው መሰረት መሬት የሚያገኙበት፤ ያገኙበትን መሬት በተገቢው መንገድና በተቀመጠላቸው ውል አማካኝነት ኢንቨስት እንዲያደርጉና ራሳቸውን ጠቅመው ሃገርንም ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሕጎች መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

«በመድረኩ ላይ እንደተነሳው በተለይ በሕጎች አፈፃፀም ላይ ችግሮች መኖራቸው የማይካድ ነው፤ የእኛ መስሪያ ቤትም በዋናነት ሕጎችን የማሻሻልና ክልሎችም ማስፈፀሚያ መመሪያዎችን አውጥተው እንዲተገብሩ ድጋፍ የማድረግ ሥራ እየሰራ ነው» ይላሉ፡፡ በተለይም ድጋፍ ከሚያደርጉ አካላት ጋር በመሆን ክልሎች የወጣውን ሕግ ተግባራዊ እንዲያደርጉ የአቅም ግንባታ ሥራዎች እየተከናወኑ ስለመሆኑም ይገልፃሉ፡፡

ከካሳ ክፍያ ጋር ተያይዞ በመድረኩ ላይ የተነሳውን የሕግ አፈፃፀም ችግር አስመልክተው ሲያብራሩ አዋጅና ደንብ በፌደራል ደረጃ ነው የወጣው፤ መመሪያ ክልሎች እንዲያወጡ ነው የሚጠበቀው ብለዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ሚኒስቴሩ ሁሉም ክልሎች መመሪያ እንዲኖራቸው ግፊት የማድረግ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አመልክተው፣ በዚህ መሰረትም አማራ ክልል፤ ኦሮሚያና ትግራይ ክልሎች ደግሞ መመሪያውን አዘጋጅተው ይፀድቃል ተብሎ እየተጠበቀ ነው፡፡ አብዛኞቹ ክልሎች አፅድቀው ወደ ተግባር አይሂዱ እንጂ ረቂቅ አዘጋጅተዋል ይላሉ፡፡

«መመሪያው ዝርዝር ነገር ያስቀምጣል እንጂ አዋጅና ደንብን ለመተግበር የሚከለክል ነገር የለም» የሚሉት አቶ አበባው፤ በዚህ መሰረትም ሚኒስቴሩ ክልሎቹ እንዲሰሩ አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ ስለመሆኑ ነው ያብራሩት፡፡

በአማራጭ ፖሊሲው የተቀመጡ አብዛኞቹን ችግሮች ሚኒስቴሩ የሚጋራቸው መሆኑን ያነሳሉ። አብዛኞቹ ከአፈፃፀም ጋር ተያይዘው የተነሱ ችግሮች በተጨባጭ መሬት ላይ የሚታዩ ስለመሆናቸው ባለሙያው ያምናሉ፡፡ ብዙዎቹ አንኳር ጉዳዮች መንግስት የግብርና ኢንቨስትመንት አሁን ካለበት ደረጃ ከፍ ለማድረግ እየሰራ ላለው ሥራ እንደግብዓት የሚያገለግሉ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ በተለይም ሕጎችን ለማሻሻል እየተሰራ ላለው ሥራ የማይናቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ያስረዳሉ፡፡ በየክልሉ ያሉ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘቡ ተጨማሪ ጥናቶች እንደሚያስፈልጉም ጠቁመዋል፡፡

ይሁንና ሕጉ ላይ የተቀመጡ ድንጋጌዎችንም በቅጡ ካለመረዳት የመነጩ አንዳንድ ሃሳቦች መኖራቸውን ያመለክታሉ፡፡ እንደ ችግር ከቀረቡት ጉዳዮች መካከል አብነት አድርገው ሲጠቅሱ «ካሳ በሚከፈልበት ጊዜ ካሳውን ባለሃብቶች ለመንግስት ነው የሚከፍሉት፤ ከዚህ በፊት ግን ካሳውን በቀጥታ ለባለይዞታ ነበር የሚከፍሉት፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተነሳውን ጉዳይ እኛ እንደ ችግር አናየውም» ይላሉ፡፡ «ምክንያቱም መንግስት ከባለይዞታውና በባለሃብቱ መካከል ድልድይ ሆኖ የማገልገል ሚና የሚጫወት በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት ያግዛል እንጂ ችግር ሊሆን አይችልም» በማለት ተናግረዋል፡፡

በፖሊሲ ሰነዱ ከተነሱ አብይ ችግሮች መካከል ከላይኛው የመንግስት አካል ጀምሮ እስከ ቀበሌ ድረስ ያለው የተንዛዛ አሰራርና ቢሮክራሲ ተጠቃሽ ነው፡፡ ይህንንም ጉዳይ በሚመለከት አቶ አበባው «ቢሮክራሲውን መቀነስ የሚቻለው በዋናነት ተጠያቂነትን ማስፈን ሲቻል ነው፤ የእኛ መስሪያ ቤት ሚና የአቅም ግንባታ ስራ መስራት ነው» ይላሉ፡፡ ክልሎች ላይ ቢሮክራሲ ሳይኖር ሥራቸውን እንዲሰሩ ሕግ የማውጣትና አቅማቸውን የማጠናከርና ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነቱን እየተወጣ ስለመሆኑም ያብራራሉ። ተጠያቂነትን ማስፈን የሚቻለውም ሚኒስቴሩ ብቻ በሚያደርገው ጥረት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሲታከልበት እንደሆነ ነው ያስገነዘቡት፡፡

በመድረኩ የተገኙት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተወካይ እንዳሉት፤ የፖሊሲ ጥናቱ በዋናነት ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ ለሚለሙ እንደ ግብርና ያሉ የኢንቨስትመንት ሥራዎች መጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በተለይ ባለሃብቱ ለኢንቨስትመንት ወደ ኢትዮጵያ ከሚጠይቃቸውና ዋነኛ ግብዓት የሆነው የመሬት አቅርቦት ላይ ያሉ ችግሮችን ለመፈተሽ ይረዳል። በሃገሪቱ ሕግ መሬትን የማስተዳደር መብት ለክልሎች የተሰጠ እንደመሆኑ በየአካባቢው ያለው የመሬት አሰጣጥም ሆነ በኢንቨስትመንት ምክንያት ለሚነሱ ባለይዞታዎች ካሳ ክፍያ አሰራር ወጥነት የለውም። ይሁንና በጥናቱ ላይ እንደተነሳው ባለሃብቶች ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ ተገማች ዋጋና ጊዜ አስቀድሞ አውቆ መስራቱ ወሳኝ ነገር እንደሆነ ይታመናል፡፡

በዚህ ረገድ የፖሊሲ ጥናቱ ወደፊት ተቋሙም ሆነ እንደሃገር ለመስራት ለታቀዱ የልማት ሥራዎች ወሳኝ ሚና እንዳለው ይናገራሉ፡፡ በተለይም ባለሃብቶች ለልማት መሬት ሲጠይቁ ያለቢሮክራሲና የተንዛዛ አሰራር በቀጥታ መሬት ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ያግዛልም ይላሉ፡፡ በተመሳሳይ ኮሚሽኑ ባለኃብቶቹ የሚያነሷቸውን ቅሬታዎች የሚቀበል መሆኑን ጠቁመው፤ ከሚነሱት ቅሬታዎች መካከል የመሬት ጉዳይ ዋነኛው እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ መሬት ከተሰጣቸው በኋላም በተለያየ ምክንያት መሬቱ ላይ ያላቸው መብት የሚጣስበት ሁኔታ መኖሩም ተወካዩ ጠቁመዋል፡፡ «ኮሚሽኑ ይህ ችግር መኖሩን ያምናል፤ መሬትን የሚመለከት ችግር የለም ማለት አይቻልም፤ ይሁንና ተቋማችን ለመፍትሔም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር አብሮ ይሰራል» ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡

«በመድረኩ የቀረቡ ምክረ-ሃሳቦች ወደፊት ለሚከናወኑት ሥራዎች ጥሩ ግብዓት ናቸው፤ እንደ ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተቀብለን የምናስተካክል ነው የሚሆነው ብለዋል፡፡ ከሕግ አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የተነሱ ችግሮችንም ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በቅንጅት እንደሚሰራም ያመለክታሉ፡፡ ተወዳዳሪ የሆነ ሃገር መፍጠር የመንግስት ቁርጠኛ አቋም መሆኑንም ጠቅሰው፣ ባለሃብቶቹ ወደ ሌላ ሃገር እንዳይሸሹ መስራት ይገባል የተባለውም ሃሳብ ሙሉ ለሙሉ የሚቀበሉት እንደሆነ ነው ተወካዩ የተናገሩት፡፡

ማህበራዊ

# አስኳላ

# አፍሪካ አንድነት - ግንባር ቀደሙ የትምህርት ተቋም

ግርማ መንግሥቴ

በአሁኑ ዘመን በትምህርት ጥራት መስፈርት መሰረት ጥራት ያለው ትምህርትን ለተማሪዎች መስጠት የሚቻለውና ተማሪዎች ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መብታቸውን የሚያረጋግጡት ከጎበዝ መምህር ብቻ አይደለም። ከመማሪያና ማመሳከሪያ መጻሕፍት ብቻም አይደለም። ወይም ደግሞ ከሁለቱም ብቻም አይደለም። በርትቶ ከማጥናት ብቻም አይደለም፤ ተማሪዎችም ሆኑ የትምህርት ተቋማት ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት ከመማር ማስተማር ከባቢም ጭምር ነው።

ከዚህ አኳያ ሲታይ በትምህርት ሚኒስቴር "አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር" (2008-2012 ዓ.ም) ሰነድ ላይ እንደተገለፀው ከ92 በመቶ በላይ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መፀዳጃ ቤት እንዳላቸው የገለፁ ሲሆን 60 በመቶ ያህሉ ግን የውሃ አቅርቦት የላቸውም። ከጠቅላላዎቹ 20 በመቶ ብቻ ክሊኒክ ሲኖራቸው፣ የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል ያላቸው ግማሾቹ ብቻ ናቸው፡፡ በስምንት ክልሎች ለመጀመሪያ ጊዜ በ2006 ዓ.ም የተካሄዱት የውስጥ ኢንስፔክሽኖች እንደሚያሳዩት የሁኔታዎች መሻሻል የታዩ ቢሆንም በአጠቃላይ ግን ትምህርት ቤቶቹ ያሉበት ሁኔታ ከሚጠበቀው በታች ነው፡፡

ይኸው ሰነድ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ጥራት ያለው አካባቢና ትምህርት ማሟላት እንዲቻል ስልታዊ ዕቅድ ማዘጋጀት እንደ ሚኖርባቸው ጠቁሟል፡፡ እያንዳንዱ የትምህርት ቤት ማሻሻያ እቅድ ውጤታማ የትምህርት ቤት ፋሲሊቲዎች ከማሟላትና ጥሩ የትምህርት አካባቢ ለመፍጠር ከማቀድ በዘለለ መሄድ እንዳለበትም ጠቅሷል፡፡ የትምህርት ቤት ማሻሻያ እቅድ ዋናና መሰረታዊ ክህሎት ለተማሪዎች በብቃት መስጠቱን ማረጋገጥ እንዳለበትም አብራርቷል፡፡

ሌሎች እንዳሉ ሆኖ ይህንን በተግባር ስራ ላይ አውሎ የታየው የትምህርት ተቋም ቢኖር አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የቅድመ አንደኛ ደረጃ (ከኬጂ 1 እስከ ኬጂ 3) እና አንደኛ ደረጃ (ከ1ኛ እስከ 8ኛ) ትምህርት ቤት ነው። ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አክሊሉ እሸቱ ጋር ያደረግነው ቆይታም የሚነግረን ይህንኑ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ ጋር በመሆን የአፍሪካ ከንቲባዎች የሊደርሺፕ ኢኒሼቲቭ (AMALI) ተሳታፊዎችን አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትን ማስጎብኘታቸውን ርዕሰ መምህር አክሊሉ ነግረውናል። "ጉብኝቱ በዋናነት በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የቀዳማይ ልጅነት ፕሮጀክት አተገባበር ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በማየት ፕሮግራሙን በቀጣይነት ለመደገፍ እንዲቻል ታስቦ የተካሄደ ነው፡፡

የጉብኝቱ ተሳታፊዎች በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ በመዘዋወር የሕጻናቱን የመማሪያ፣ የመጫወቻ እና የማሸለቢያ ክፍሎች፣ መጎብኘታቸውንም በወቅቱ ከወጡ መረጃዎች ለማወቅ ችለናል። የአፍሪካ ሕብረት አዲስ አበባ መመስረትን ተከትሎ በተቋቋመውና ስያሜውንም ከዚሁ ጋር በማያያዝ የተሰየመው አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በትምህርት አመራሮች አማካኝነት አዲሱን ስርዓተ ትምህርት መሰረት አድርጎ የተዘጋጀውን የቅድመ አንደኛ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለከተማው ትምህርት ቢሮ ሱፐርቫይዘሮች የማስተዋወቅ ስራ መሰራቱንም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህም በትምህርት ቤቱ ተገኝተው ተቋሙን



ርዕሰ መምህር አክሊሉ እሸቱ፡፡

ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

በመጎብኘት አድናቆታቸውን መግለፃቸውን ርዕሰ መምህር አክሊሉ ነግረውናል። አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስለ ውጤታማነቱ የተመሰከረለት መሆኑን የሚናገሩት ርዕሰ መምህሩ "የአንድ ተቋም መመዘኛ በአብዛኛው በብሄራዊ ፈተናዎች በሚያሳልፉቸው ተማሪዎች ሲሆን በዚሁ መነሻነት ትምህርት ቤቱ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ በዘንድሮው የአንደኛው ወሰነ ትምህርትም 98 ነጥብ 8 በማምጣት ውጤታማነቱን አሳይቷል፡፡

ከተገልጋይ እርካታ አኳያም አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የሚያስመሰግን ውጤት ማግኘቱን ከርዕሰ መምህሩ ቢሮ የተገኙ መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፣ የ2015 ዓ.ም የአንደኛ ሩብ ዓመት የውስጥ 98 ነጥብ 6 ከመቶ እና የውጭ 97 ነጥብ 4 ከመቶ፤ እንዲሁም የተመሳሳይ ዘመን ሁለተኛ ሩብ ዓመት የውስጥ 98 ከመቶ፤ የውጪ 98 ነጥብ 2 ከመቶ የተገልጋይ እርካታ ዳሰሳ ትንተና ውጤቶች ማሳያዎች ናቸው።

የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ታህሳስ 2016 ዓ.ም "ፅዳቱ የተጠበቀ የመማሪያ ስፍራ፣ ለመማር ማስተማር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል" በሚል መሪ ቃል የአምስት ወራት ሳምንታዊ የፅዳት ንቅናቄ ዘመቻ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር በክፍለ ከተማው ወረዳ አራት በሚገኘው በኡላዱላ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አካሂዷል፡፡ "ጽዱና ውብ ትምህርት ቤት ለተማሪዎች!" በሚል መሪ ቃል የጽዳት ንቅናቄ ፕሮግራም አካሂዷል፡፡

አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ለምሳሌ በጉለሌ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 7 አስተዳደር ስር የሚገኘው "ሐምሌ አስራ ዘጠኝ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት" እና ሌሎችም አፍሪካ አንድነት ቁጥር ሁለትም እንደዚሁ የፅዳት ፕሮግራሞች አሏቸው። ተማሪዎቹ ምንም አይነት ቆሻሻን በጊቢ ውስጥ ላለመጣል፤ ተጥሎም ካገኙ አንስቶ ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ በመጣል ለትምህርት ቤቱ ፅዱና ማራኪነት የበኩላቸውን እየተወጡ መሆናቸውን ርዕሰ መምህር አክሊሉ ይናገራሉ።

የሥነ-ትምህርት ባለሙያዎች የሚሰጡት ትምህርት ውጤታማ እንዲሆን፤ የትምህርት ጥራት እንዲረጋገጥ፤ የተማሪዎች ስነ-ምግባር እንዲሻሻል፤ ሁለንተናዊ የመማር-ማስተማር ስራው የላቀ ደረጃ ላይ እንዲደርስ በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት

**አሁን ባለው ሁኔታ ይህ ብዙም አይታይም። በመሆኑም የወላጆች የቅርብ ክትትልና እገዛ ለትምህርት ተቋማት መሻሻል እጅግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው**

አመራሮች ተከታታይነት ያለው ድጋፍና ክትትል በማድረግ በትኩረት መስራት እንደሚገባቸው መምህር አክሊሉ ያሰምሩበታል። ከዚህ አኳያ የአፍሪካ አንድነት ቁጥር ሁለት የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በየደረጃው ያሉ ሁሉ ለትምህርት ጥራት ይበጃል ያሉትን እየሰሩ እንዳሉ በርዕሰ መምህሩ ከመገለፁ በተጨማሪ እኛም ተዘዋውረን ተመልክተናል።

1 ሺህ 653 ተማሪዎችን የሚያስተናግደው ይህ ትምህርት ቤት አመራሮችና መምህራን ከተማሪና ወላጅ አደረጃጀት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር በ"ትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ" የተጀመረውን የትምህርት ተቋማትን ደረጃ የማሻሻል ስራ ውጤታማ እንዲሆን በትኩረት እየሰሩ መሆናቸውንም ርዕሰ መምህሩ ይናገራሉ።

የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ወደ መንግሥት እንዲዛወሩ በሚደነግገው አዋጅ መሰረት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ወደ መንግሥት ትምህርት ቤትነት በተዛወረው፣ በአፍሪካ አንድነት ቁጥር ሁለት የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃውን የጠበቀ "ሁለ-ገብ" የስፖርት ማዘውተሪያ መገንባቱን የተናገሩት ርዕሰ መምህር አክሊሉ፤ የግንባታው ወጪ የተሸፈነው በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ "መደመር" መጽሐፍ ጭያጭ ከተገኘው ገቢ መሆኑንም ገልፀዋል።

በፊት ነበር እንጂ አሁን በአብዛኛው የግብአት ችግር የለብንም የሚሉት ርዕሰ መምህር አክሊሉ እሸቱ፤ በትምህርት ቤቱ በሁለት ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ እና አፋን ኦሮሞ ትምህርቶቹ የሚሰጡ ሲሆን በአፋን ኦሮሞ በሚሰጡ የትምህርት አይነቶች በኩል የተወሰነ የግብአት እጥረት እንዳለም ይናገራሉ።

አፍሪካ አንድነት ቁጥር ሁለት የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ቅድመ መደበኛ ትምህርትንም የሚሰጥ ተቋም እንደ መሆኑ መጠን ጥራቱን የጠበቀ፤ ለሌሎች በምሳሌነት ሊቀርብ የሚችል፤ ፅዳቱ የተሟላና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጠውን መስፈርት ባሟላ መልኩ ሕፃናትን (ከኬጂ 1 እስከ ኬጂ 3) እያስተማረ ይገኛል።

ኬጂ 1 እና 2 ተማሪዎች ያማረ ምንጣፍ ላይ እንደ ፈለጋቸው፣ ተገቢ ባለሙያ ተመድቦላቸው እየተንከባለሉ የሚያነቡ፣ የሚፅፉና የሚጫወቱ መሆናቸው የተነገረንና እኛም የተመለከትን ሲሆን፤ ከምሳ በኋላም ለአንድ ሰዓት ያህል የእንቅልፍ ሰዓታቸውን የሚያሳልፉበት ያማረ መኝታ ክፍል ከተሟላ ፍራሽና ትራስ ጋር መሰናዳቱን ተመልክተናል። ይህም በራሱ ሌሎች ሊወስዱት የሚገባ ተሞክሮ ነው፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ተቋሙን በጎበኙበት ወቅት "በአዲስ አበባ የአፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 ቅድመ አንደኛ፣ የመጀመሪያ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከናወኑ የልማት ሥራዎች ለሌሎችም ትምህርት ቤቶች ተሞክሮ የሚሆኑ ናቸው። በማለት ምስክርነታቸውን የሰጡለት አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 ቅድመ አንደኛ፣ የመጀመሪያ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በብዙ መልኩ በተሻለ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል።

ርዕሰ መምህር አክሊሉ እንደሚሉት ደግሞ አንዳንድ - ለምሳሌ የላቦራቶሪ፣ ቤተመጻሕፍት፣ አይሲቲ (ኮምፒውተር) እና የመሳሰሉትን ክፍተቶች ለመሙላትና ከተማሪዎቹ ቁጥር ልክ ለማድረስ ባለ ሀብቶችን በማስተባበር አንዳንድ ስራዎች በመሰራት ላይ ይገኛሉ።

ምቹ የምገባ አዳራሽ የሌላቸውን ትምህርት ቤቶችን ልበ ቀና ባለሀብቶችን በማስተባበር በአጭር ጊዜ አጠናቆ ለአገልግሎት ክፍት ለማድረግ በትኩረት እየሰራ መሆኑን የሚናገረው የየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር "አሻራችንን በማኖር የየካን ከፍታ እናረጋግጥ" በሚል መሪ ሀሳብ 4ኛ ዙር የ90 ቀናት ሰው ተኮር ፕሮጀክት አካል የሆነው የኮተቤ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ምገባ አዳራሽ ግንባታ ታህሳስ 17 ቀን 2016 ዓ.ም የመሰረት ድንጋይ ተቀምጧል፡፡

"የመመገቢያ አዳራሽ እጥረት አለብኝ" እያለ ላለውና ከባለ ሀብቶች ጋር እየመከረ ስላለው አፍሪካ አንድነት ቁጥር 2 የቅድመ አንደኛ ደረጃ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ተመሳሳይ እድል እንደሚገጥመው ተስፋ ማድረግ ይቻላል።

ወላጆችን በተመለከተ አስተያየታቸውን የሰጡን ርዕሰ መምህሩ እንደሚሉት ትምህርት ቤት መመራት ያለበት በወላጅ ነው። ይሁን እንጂ ወላጆች ከትምህርት ቤቱ አመራርና መምህራን ጋር እጅ እና ጓንት ሆኖ መስራት ላይ የተወሰኑ ክፍተቶች አሉ። መምህራን ምን ግዜም ከትምህርት ቤት መለየት የለባቸውም። ስለልጆቻቸው በቅርብ በመከታተል ማወቅ አለባቸው። መምህራንን ማማከርና ችግር ካለ በመነጋገር መፍታት ይገባቸዋል።

አሁን ባለው ሁኔታ ይህ ብዙም አይታይም። በመሆኑም የወላጆች የቅርብ ክትትልና እገዛ ለትምህርት ተቋማት መሻሻል እጅግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ይህ በግል ትምህርት ቤቶች በኩል ሻል ባለ ሁኔታ ሲታይ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ግን ብዙም አይታይም እና ወላጆች ስለልጆቻቸው የቅርብ ክትትል ማድረጉ ላይ ችላ ሊሉ አይገባም።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ ሕዝብና መንግስት የጣለብንን ሕግ የማስከበር ተግባር እየተወጣን ነው ››

- አቶ ተክሌ በዛብህ - የአዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮ ኃላፊ

እፀገነት አክሊሉ

መሰረታዊ ከሚባሉ የሰው ልጆች ፍላጎቶች መካከል ፍትህ ግንባር ቀደሙን ቦታ ይይዛል። በእርስ በእርስ አለመግባባትም ይሁን በሌላ ጉዳይ ሰዎች ፍትህን ሲሹ ይችላሉ ፡፡ ይህንን ፍትህ ሊያስከብር የሚችል በዳይን የሚጠይቅ ተበዳይን የሚክስ ተቋም ደግሞ እጅግ አስፈላጊ ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮም መንግስትና ሕዝብ የጣሉበትን ፍትህን የማስከበር ስራ እያከናወነ ይገኛል። እኛም ከቢሮ ኃላፊው ከአቶ ተክሌ በዛብህ ጋር ቆይታን አድርገናል።



ፎቶ፡- አሸናፊ ጉደታ

**አዲስ ዘመን፡- የአዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮ ከዚህ ቀደም በነበረው ሁኔታ አደረጃጀትና ሂደቱ ምን ይመስል ነበር?**

**አቶ ተክሌ ፡-** ቢሮው በ1995 ዓ.ም በፊት ጀምሮ ባለው ሁኔታ የአቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ይባል ነበር። በኋላም በ1995 ዓ.ም በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361 ላይ አንቀጽ 28 መሰረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት በሚል ተደንግጓል። ይህ ሲታወጅ ሁለት ንዑሳን አንቀጾች የነበሩት ሲሆን አንደኛው በከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮችን የመከራከር ወይም የማየት፤ የማቅረብ ኃላፊነት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ስልጣንና ተግባሩ በሌሎች ጉዳዮች ላይ በሚወጡ ዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ ሆኖ በአዋጅ ይወጣል በሚል የተቀመጠ ነው።

ከዛም በአዋጅ ቁጥር 4/2000 ላይ የፍትህና ሕግ ጉዳዮች ቢሮ በሚል የሰራተኛና አሰሪ እንዲሁ ማኅበራዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማካተት የፍትህና የሕግ ቢሮዎች በሚል በአዋጅ ቁጥር 4/2000 ላይ ተደራጀ ። ከዛም ከአንድ ዓመት በኋላ በአዋጅ ቁጥር 15 /2001 ላይ ፍትህ ቢሮ የሚለውን ስም ይዟል። በዚህም የደንብ ማስከበር ጽህፈት ቤትና የማኅበራዊ ፍርድ ቤት አስተዳደር ጉባኤ ጽህፈት ቤትን በማካተት እንዲደራጅ ይሆናል።

በዚህ ሳያበቃ ከ 3 ወይም 4 ዓመት በኋላ በአዋጅ ቁጥር 35 /2004 ላይ ከላይ የተጠቀሱትን ተቋማት በመያዝ ዳግም ፍትህ ቢሮ በሚል ስያሜ ተቋቁሟል። በዚህ ሁኔታ ቆይቶ ከአዲሱ ለውጥ ማግስት አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ኃላፊነት ለመደንገግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 መሰረት የጠቅላይ አቃቤ ሕግ ቢሮ በሚል ብቻውን ተደራጅቷል።

ከላይ ያነሳናቸውን ተጠሪ እንዲሁም አብረው ሲደራጁ የነበሩትን ተቋማት አውጥቶ ከሁለት ዓመት በኋላም አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ኃላፊነት ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ሲሻሻል በአዋጅ ቁጥር 74 /2014 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ ይግባኝ ተቋምን ይዞ ፍትህ ቢሮ በመሰኘት ተደራጅቷል። በዚህ ዓመት አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ኃላፊነት ለመተካት የወጣው አዋጅ ቁጥር 84/2016 መሰረትም ከላይ የተገለጸውን ተጠሪ ተቋም ይዞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ በሚል ተደራጅተቶ ስራ ላይ ይገኛል።

**አዲስ ዘመን ፡- በዚህ ሂደት ውስጥ በተለይም ተገልጋይን በማርካት በኩል የመጡ ለውጦች እንዴት ይገለጻሉ?**

**አቶ ተክሌ ፡-** የከተማዋ ነዋሪ ያለው የፍትህ ጥማትና ፍላጎት እንዲሁም የሕግ የበላይነት እውን እንዲሆንም ይፈልጋል። ከተማ አስተዳደሩም ይህንን በመረዳት ከከተማዋ ከፍ ብሎ አዲስ አበባ የአህጉሩ ጽህፈት ቤት መቀመጫ እንዲሁም የተለያዩ ዲፕሎማቶች መቀመጫነቷን ታሳቢ ያደረገ ስራን ነው የሚሰራው። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር አዲስ አበባ ከተማ ከሁለት የዓለማችን ትልልቅ ከተሞች በመቀጠል ሶስተኛዋ የዲፕሎማቲክ ከተማ ሆና ነው የምትታወቀው። ከዚህ አንጻር የሕግ የበላይነት ከፍ ባለ ሁኔታ እንዲከበር ተቋሙ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ተደባልቆ የሚፈለገውንም ለውጥ ሳያመጣ ስያሜውም ሳይጎላ ብዙ ትርጉም ያለው ስራ ሳይሰራ መቆየቱ የሚታወቅ ነው።

በመሆኑም የከተማዋ ነዋሪዎች ያልተመለሰ የፍትህ ጥያቄ ተቋሙም ራሱን እንዲያይና ወደ ሪፎርም ስራ እንዲገባ ምክንያት ሆኗል። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ብቃት ባለው የሰው ኃይል የተደራጀና ተቋማዊ ቁመናን የያዘ ሆኖ እንዲደራጅ ከመፈለግ አንጻር ኃላፊነቱና ተልዕኮውም ከበፊቱ በተሻለና ጥርት ባለ ሁኔታ ተዘጋጅቶ ተቋሙም በዛ ሁኔታ ነው የተደራጀው። ይህንንም ለማሳካት ከዚህ በፊት በአስፈጻሚ አካላት ዘንድ ተገልጸው የማያውቁ ዘርዘር ያሉ የስራ ድርሻና ኃላፊነቶች ተቀምጠውለታል።

በተለይም ከለውጡ ወዲህ በወጡ አዋጆች ላይ በዝርዝር ተቀምጠው ይገኛሉ። ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ የሰው ኃይልን በሚፈለገው ልክ የማደራጀት ተቋማዊ ቁመና የማላበስና በቴክኖሎጂ የማዘመን ስራም ያስፈልግ ስለነበር ይህንን በማሳለጥ በኩል ከተማ አስተዳደሩ ትልቅ ስራ ሰርቷል።

ይህ ተቋም በሰው ኃይል በኩል ሰፊ ክፍተት የነበረበት ባለሙያዎቹ ተረጋግተው የማይሰሩና ከፍተኛ የሆነ የሰራተኞች ፍልሰት የነበረበት ከመሆኑ ጋር በተያያዘ መፍትሔ ለመስጠት ከ 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተቋሙ ራሱን ችሎ የሚመራበት ደንብ ወጥቶለታል። ይህንን ደንብ ተከትሎ የጉባኤ ጽህፈት ቤት አቃቤ ሕግ የስነምግባር (ዲስፒሊን) የቅጥርና ዝውውር እንዲሁም ሌሎች መሰል ተግባራትን የሚወስን ጉባኤ ጽህፈት ቤት ተደራጅቷል።

ደሞዙም አገራዊ ሁኔታን እንዲሁም የሌሎች ክልሎችን ስኬል በተከተለ መልኩ ከፍ እንዲል በማድረግ ባለሙያዎች ተረጋግተው የሚሰሩበትን የስራ አካባቢ በመፍጠር በኩል ትልቅ ስራ ተሰርቷል። ይህ መሆኑ ደግሞ ገበያው ላይ ተወዳዳሪና ጥራት ያለው የሰው ኃይልን ለማግኘት ያስቻለ ከመሆኑም በላይ ለተቋሙ ጥንካሬም ከፍ ያለ አስተዋጽዖን አበርክቷል።

ይህንን ተከትሎ በሰው ኃይል ቁጥርም ሆነ ጥራትና ብቃት ከማሳደግ አንጻር ትልቅ ስራ ነው ብሎ መውሰድ የሚቻል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በማዕከል ደረጃ 56 የሚሆኑ አቃቤ ሕጎች ይገኛሉ፡ ፡ በክፍለ ከተሞች ደግሞ 418 የሚደርሱ አቃቤያነ ሕጎች ያሉ ሲሆን የቅጥራቸው የዝውውራቸው እንዲሁም ሎሎች ጉዳዮቻቸው የሚታየው በማዕከል መሆኑም ሊታወቅ ይገባል።

በጠቅላላው 747 አቃቤ ሕጎች በስራ ላይ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ በጥናት ምን ያህል የሰው ኃይል የሕግ ጉዳዮቹን ማካሄድ ይችላል የሚለውን ባማከለ መልኩ ወደ 77 በመቶ ገደማም መሸፈን የቻለ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን የተቋሙን አቅም ከማሳደግ አንጻር ለባለሙያዎች አጫጭርና ረጃጅም ስልጠናዎችን እየሰጠን መጥተናል፡፡

**21ሺ 786 በሚደርሱ መዝገቦች ላይ መርታት ተችሏል። ይህ ውጤት በገንዘብ ሲተመን 7 ነጥብ 9 ቢሊየን ብር ገደማ የሕዝብና የመንግስት ጥቅምን ማስጠበቅ ችለናል**

በሂደትም በተለያዩ ምክንያቶች ለብልሹ አሰራር የሚጋለጡ ባለሙያዎችንም ተጠያቂ በማድረግ በኩል ትልቅ ስራ ተሰርቷል።

ተቋሙ ራሱን በሰው ኃይልም ሆነ በቴክኖሎጂ ሲያዘምን ዋናው ዓላማ የከተማዋን ነዋሪ የፍትህ ጥያቄ መመለስ ነው። በዚህም ሕዝቡ በተለይም ከለውጡ ወዲህ በሚሰጠው አገልግሎት ምን ያህል ረክቷል በሚል የፌዴራል ሕግና ፍትህ ኢንስቲትዩት የዳሰሳ ጥናት አድርጓል፤ የሕዝቡ እርካታ ከ60 በመቶው ያልበለጠ መሆኑን ደግሞ ውጤቱ ያሳያል።

ይህንን በመያዝም በአዲስ አበባ ከተማ ፍትህ ቢሮ ሊሰሩ የሚገቡ ተግባራት ዘርዝረው ከላይ በጠቀስኳቸው ህጎች ለእኛ የተሰጡን ሰልጣኖችን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር መሰረታዊ የሚባሉ ስራዎችን እየሰራን ውጤትም እያገኘን እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ አንጻር በተቋሙ ላይ የተሰራው የሪፎርም ስራ ለውጥ አምጥቷል ማለት ይቻላል?**

**አቶ ተክሌ፡-** በእርግጥ ሂደቱን በአንድ ጊዜ መገምገም የሚቻል ባይሆንም ጥሩ እንደሆነ መናገር ይቻላል። እዚህ ላይ አንደኛው መለኪያችን የነበረው አገልግሎት ወሳጁ የከተማ ነዋሪ መሆኑ ሲሆን ሌላው ደግሞ የእርካታ ዳሰሳ ጥናትና ከተለያዩ አካላት የሚመጡ ጥቆማዎች ናቸው፤ ይህ አሰራር ደግሞ እስከ አሁንም የቀጠለበት ሁኔታ ነው ያለው። ከዚህ በተጨማሪ ግን ብቃት ያለውን ክስ የመመስረት የመከራከርና ድርድር የማድረግ አቅም ያለው የሰው ሃይል እንድናደራጅ መንገድ ከፍቶልናል። ከለውጡ ወዲህ ተቋሙ ራሱን ችሎ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ በህግ እንዲመራ ስርዓት ተበጅቶለታል። ይህንን ተከትሎ የተቋሙን የሰው ኃይል ቁጥርም ብቃትም ከማደራጀት አንጻር መጠነ ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል።

ሌላው ተቋሙን በዘመናዊ ቴክኖሊጂ የማደራጀት ሂደት ምንም እንኳን ጅምር ላይ ያለ ቢሆንም ከዚህ በፊት በተለያዩ ስያሜዎች እየተጠራ በህዝቡ ውስጥ መግባት ሳይችል መቆየቱን ታሳቢ በማድረግ ስሙን የማጉላት ስራዎችን የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ሰርተናል። ይህንንም በቀጣይ በምናረቃቸው ሕጎች ? ክርክር በምናደርግባቸው ጉዳዮች ምን ያህል ውጤታማ ይሆናሉ የሚለውን ከዚህ ጋር አያይዞ ማንሳት ይቻላል። ከዚህ አንጻር ከለውጡ ወዲህ በተቋሙ ላይ የተሰራው ስራ ትልቅ ውጤት እያስመዘገበ ሲሆን የከተማዋን ነዋሪ እንዲሁም የመንግስት ተቋማትን ወክለን

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ ሕዝብና መንግስት የጣለብንን...

ከ9ኛው ገጽ የዞረ

በምናደርጋቸው ክርክሮች ላይ ይበል የሚያሰኙ ተጨባጭ ውጤቶችን እያየን እንገኛለን።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ ከስውጥ ስራው ጎን ስጎን እንደ ከተማ የምንተዳደርባቸውን ህጎችና ደንቦች እንዲሁም ሌሎችን በማርቀቅና በማዘጋጀት ብሎም አጽድቆ ተግባራዊ በማድረግ በኩል ያስበት ቁመና እንዴት ይታያል?**

**አቶ ተክሴ፡-** ደንብ ቁጥር 125 /2014 ትን ጨምሮ አራት ያህል ተቋሙ ራሱ የሚመራባቸውን ደንቦችን ሰባት ያህል መመሪያዎችን ዘርግተናል ። በዚህም በዘፈቀደ ይመራ የነበረውን በሕግ እንዲመራና ተጠያቂነት እንዲሰፍን በማድረግ በኩል ስራዎች ተሰርተዋል ።

ይህንን ተከትሎም በከተማ አስተዳደሩ የፍትህ ሂደት ላይ የሚስተዋሉ በርካታ የአሰራር ክፍተቶችን ለማሻሻል አጫጭር ጥናቶችን የሕግ ማሻሻያ ስራዎችን መስራት እንዳለ ሆኖ ሶስት ግዙፍ ጥናቶችን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተጋገዝ አስጠንተናል። እነዚህ ጥናቶች ከጥናትነት ባሻገር የሚያስገኙት ፋይዳ ምንድነው ? የሚለውን የመዳሰስ ማንዋሎች እንዲዘጋጁ የማድረግ ባለሙያዎቻችን በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የነቃ ተሳትፎን እንዲያደርጉ የማድረግ ስራዎች ተሰርተዋል።

በሌላ በኩልም እንደ ከተማ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ 20 አዋጆችን 52 ደንቦችንና 295 መመሪያዎችን የማርቀቅ ስራዎች ተሰርተዋል። ለህብረተሰቡም እንዲዳረሱ ግልጽ በሆኑ ፐላት ፎርሞች እንዲዘረጉ ሆኗል። ይህ ሁሉ ስራ በዚህን ያህል ደረጃ ሊሰራና መልክ ሊይዝ የቻለውም በመጀመሪያ ደረጃ ለውጡ እንዲመጣ በራሱ የሆነው የህዝቡ የፍትህ ጥያቄ እንደመሆኑ በሕዝቡ ዘንድ ተጨባጭና ለውጥ የሚያመጣ እንዲሆን ከተማ አስተዳደሩ በበላይነት በመያዝና በቁርጠኝነት በመስራቱ ነው።

ተቋሙ በዋናነት ከሚሰራቸው ስራዎች መካከል ክፍተት ባለባቸው ሕጎች ዙሪያ ጥናት ማድረግ ነው፤ በዚህም ክፍተት ያለባቸው ነባር ሕጎች እንዲሻሻሉና እንዲተኩ ይደረጋል። አዳዲስ የሕግ ማዕቀፍ የሚያስፈልጋቸው በተለይም በተቋማት ጥያቄና በመስሪያ ቤቱ ተነሳሽነት የሚወጡ ሕጎች አሉ። በመሆኑም እኛ የሕጉን ረቂቅ አዘጋጅተን ለሚመለከተው አካል በማቅረብ በካቢኔው ውሳኔ የሚያገኙ መመሪያዎች ሂደቱን ካለፉ በኋላ ለሕዝቡ ይፋ የሚሆኑበት እንዲሁም ለሕትመት በቅተው ተደራሽ የሚደረጉበት ሁኔታ ይሰራል።

ሕዝቡ ጋር በይበልጥ ተደራሽ እንዲሆኑም ከሕትመት ባሻገር የተለያዩ የማኀበራዊ ሚዲያ አማራጮችን እንጠቀማለን፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን ሕጎቹን የማስገንዘብና የማስረጽ ተግባር ተቋሙን የሚመለከት በመሆኑ በዳይሬክቶሬት ደረጃ የተለያዩ ክፍሎችን በማቋቋም ስራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል። ሌላው የተቋሙ ትልቅ ስራ ክርክር ማድረግ እንደመሆኑ ክርክሮች ሲደረጉ ቆይተዋል ፡፡

በዚህም ተቋማት ይከሳሉ እንዲሁም ይከሰሳሉ ይህንን ተከትሎም ተቋማት የክሰሱልኝ ጥያቄ ሲያቀርቡ መረጃዎች ተሰባስበውና መዝገብ ተደራጅቶ በሚላከው መሰረት ተቋሙ ተገቢና ትክክለኛ ክርክሮችን ያደርጋል። ከክርክር ባሻገር ድርድርም ይደረጋል። ይህም የማያዋጣ ከሆነ አቃቤ ሕጎች ተወያይተው ፋይል የመዝጋት አልያም ክስ የማቋረጥ ስራም ይሰራል። በዚህም ባለፉት አምስት ዓመታት ወደ 28 ሺ 521 የፍትህብሔር መዝገቦች ክርክር ያደረግንባቸው ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 21ሺ 786 በሚደርሱ መዝገቦች ላይ መርታት ተችሏል። ይህ ውጤት በገንዘብ ሲተመን 7 ነጥብ 9 ቢሊየን ብር ገደማ



**በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት የወንዝዳር ፕሮጀክቶችን ቸርችል ላይ የተሰሩ የልማት ስራዎችን እንዲሁም የጫካ ፕሮጀክቶችንን በሌሎች አልሚዎች የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን አስመልክቶ የሚመጡ በርካታ እግዶች ያሉ በመሆኑ እነዚህን በፍርድ ቤት ክርክር በማድረግና በአጠረ ጊዜ እንዲመለሱ በማስቻል ስራዎችን ሰርተናል**

የሕዝብና የመንግስት ጥቅምን ማስጠበቅ ችለናል።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ውጤቶች መመዝገባቸው ጥሩ ነው ነገር ግን ይህ ትልቅ የሕዝብና የመንግስት ኃላፊነትን የተሸከመ ተቋም በሰራቸው ስራ ፍትህ በማስፈን በኩል ምን ደረጃ ላይ ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ ተክሴ ፡-** ተቋሙ የሚከውናቸው 27 የሚደርሱ ዋና ዋና ተልዕኮዎች አሉት፡፡ በዋናነት ደግሞ ከተማ አስተዳደሩ በሕግ ጉዳዮች ላይ አማካሪ ነው። በከተማ አስተዳደሩ ስር ያሉ ተቋማት በሚከሰሱበት ጊዜ መልስ የሚሰጥ፤ መክሰስ ባለባቸው ጊዜ ተቋማቱን በመወከል ክስ የሚያቀርብ ነው። ከዚህ በተጓዳኝም ምክሮችን በቃል በጽሁፍ የሚያቀርብ ነው የሚሆነው። እዚህ ላይ ግን ምክርን በቃልና በጽሁፍ የምናቀርበው ለተቋማት ብቻ ሳይሆን የፍትህ ጥማት ላለባቸው ነገር ግን በአቅም ውስንነት ምክንያት ባለሙያ ማማከር ላልቻሉ ግለሰቦችም ነው።

ይህ ደግሞ እንደ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ በከፍተኛ ኃላፊነትና በቁርጠኝነት የምንሰራው ስራ ከመሆኑም ባሻገር የትኛውም የአቅም ውስንነት ሰው በተለይም ሴቶች ሕጻናትና አረጋውያን የሕግ ድጋፍ ፈልገው ቢመጡ ምን ጊዜም በራችን ክፍት መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ማሳወቅ እፈልጋለሁ።

ከዚህ ውጪ በሌሎች አማራጮች በተዘረጉ ቅሬታ፤ ጥቆማ መቀበያ የስልክ አድራሻዎችና በሌሎች መንገዶችም የሚመጡ ጉዳዮችን ለመፍታት ቅድሚያ ሰጥተን እየሰራን ነው። በሌላ በኩልም ከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ያሉ አስፈጻሚ ተቋማት በሙሉ የአሰራር ስርዓት ለማሳለጥ ውጤታማ ተግባርን ለማከናወን እንዲያስችላቸው የሚያግዟቸውን የሕህግ ሃሳቦች እናረቃለን። ከተማ አስተዳደሩ ላይ የግዢ የግንባታ እንዲሁም የዜጎችን ሕይወት እንዲቀይሩ በሚሰሩ የልማት ስራዎች ዙሪያ ከውጭም ከአገር ውስጥም በሚገቡ ውሎች ዙሪያ ምርመራ ይደረጋል። ተቋማትም እንዲያጸድቁ ተገቢ የሆነ የሕግ አስተያየትን እንሰጣለን።

መንግስትን ያልተገባ ወጪ ሊያስወጡ የሚችሉ ውሎች በሚኖሩበት ጊዜ አስተያየት እንሰጣለን፤ በመሆኑም የሚሰሩ የልማት ስራዎች በሙሉ በዚህ ቢሮ ማለፋቸው የግድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በተለይም ስራዎችን የሕግ ድጋፍ ሰጥቶ ከማሳለጥ አንጻር ሰርቻቸዋለሁ የሚለው ስራ ማሳያ ማንሳት እንችል ይሆን?**

**አቶ ተክሴ ፡-** አዎ እንችላለን ። ለምሳሌ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አነሳሽነት የወንዝዳር ፕሮጀክቶችን ቸርችል ላይ የተሰሩ የልማት ስራዎችን እንዲሁም የጫካ ፕሮጀክቶችንን በሌሎች አልሚዎች የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን አስመልክቶ የሚመጡ በርካታ እግዶች ያሉ በመሆኑ እነዚህን በፍርድ ቤት ክርክር በማድረግና በአጠረ ጊዜ እንዲመለሱ በማስቻል ስራዎችን ሰርተናል። ይህ ሲሆን ደግሞ የመንግስትን ስራ ከማሳለጥ ባሻገር ዜጎች ሳይጎዱ የሚገባቸውን ይዘው አካባቢውን ለልማት ክፍት እንዲያደርጉ በዚህም መብቶቻቸው ተጠብቀው ልማቱ እንዲቀጥል የማድረግ ስራ ተሰርቷል።

ይህ እንግዲህ በአንድ ጎን የዜጎችን ሕይወት የሚቀይሩ የልማት ስራዎች ከመሆናቸውም በላይ ከተማዋ ሊኖራት የሚገባውን ገጽታ እንድትይዝ ብሎም ከልማቱ ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር ትልቅ ሚና ያለው ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- ስራውን ከማሳለጥ አንጻር ተቋሙ ያጋጠመው ተግዳሮት እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ተክሴ፡-** በዋናነት የሚነሳው በፍትሃብሄር ጉዳዮች ላይ በብዛት እንከራከራለን፡፡ ልምድ ያላቸው በርካታ ባለሙያዎችም አሉን፡፡ እነሱም ተረጋግተው ኃላፊነታቸውን ይወጡ ዘንድ የከተማ አስተዳደሩ አስፈላጊውን ኃላፊነቱንም ተወጥቷል ማለት ይቻላል። በዚህም ደመወዛቸው ወቅቱን ያገናዘበ ሆኗል። በሌላ በኩልም የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ስነስርዓት ተከትሎ ባለሙያዎች ስነስርዓት ያለው አለባበስ እንዲለብሱ ከማድረግ አንጻር ሁሉም ክፍለ ከተማ በማዕከል ያሉ አቃቤ ሕጎችም የአልባሳት ግዢ እንዲፈጸም ተደርጓል።

ነገር ግን የፍትሐብሔር ላይ እየተከራከርን ወንጀል ነክ ጉዳዮች ቢያጋጥመን እኛ መክሰስ የምንችለው ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ በመሆኑ የነዋሪውን የፍትህ ፍላጎት ሙሉ በሙሉ እንዳናሳካ እንቅፋት ሆኖብናል። የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን ቢኖረን ውጤታማ የሆነ ስራን እንሰራ ነበር። ይህ እንግዲህ ከቻርተሩ ጀምሮ የተቀመጠና የተቀላቀለ ነገር ነው፤ አዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለፌደራል ፖሊስ የስራ ድርሻውን እንዲሁም የበጀት አመዳደቡን የሚያጸድቀው ከተማ አስተዳደሩ ተጠሪነቱ ለፌደራል ፖሊስ ይላል ።

የከተማው አቃቤ ሕግ ቀጥታ በወንጀል ጉዳዮች ላይ የማዘዝ ስራዎችን ከመፈጸም አንጻር ውስንነቶች አሉበት፡፡ በመሆኑም እነዚህ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በፍትህ ዘርፍ ከጀመረው ትራንስፎርሜሽን ስራ በከተማ አስተዳሩም እየተመራ ስለሆነ በዚህ መሰረት አንዳንድ ማሻሻያና ማስተካከያዎች ይደረጋሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ከዚህ ባሻገር የተለያዩ የአቅም ግንባታዎች እየተደረጉ ቢሆንም ዛሬም ድረስ ያልተፈታውና ተቋሙን በተለያየ አይነት ስም የሚያስነሱ የተወሰኑ ሰዎች ላይ ቢሆንም የስነ ምግባር ጥሰቶች አሉ፤ ይህንንም ለመፍታት እየሰራን ቢሆንም አሁንም ከችግሩ ስላልወጣን የተጠናከረ ስራን መስራት እንደሚፈለግብን እንገነዘባለን።

ከሀብት ውስንነት አንጻር ቴክኖለሎጂ ላይ የሚስተዋሉ ውስንነቶች አሉ ነገር ግን ወደፊት ስራዎች ከእጅና ከወረቀት ንክኪ ነጻ ይሆኑ ዘንድ ስራዎችን በቴክኖሎጂ ለመስራት ከፍ ያለ ጥረትን እያደረገን እንገኛለን።

ሕብረተሰቡ በተለያዩ የሕትመት ውጤቶች ሕጎች ይወጣሉ፡፡ እንዲያውቁትም ጥረት ይደረጋል፡ ፡ ነገር ግን ይህ ብቻውን በቂ ባለመሆኑ ተቋሙ ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር በመተባበር ሕጎችን የማስረጽ ስራን እየሰራ ነው። ይህም በቂ ባለመሆኑ በቀጣይም ሌሎች አማራጮችን ለማየት እንሰራለን ።

**አዲስ ዘመን ፡- የቢሮው ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎችስ ምንድን ናቸው?**

**አቶ ተክሴ፡-** ቢሮው አርዓያ የሆነ የፍትህ ተቋም መገንባትን ግብ አድርጎ ነው የሚንቀሳቀሰው ፤ ይህንን ለማሳካትም በብቃትና በስነ ምግባር የበቃ የሰው ኃይል የማፍራት ስራ ይሰራል። ለዚህም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በከፍተኛ ማዕረግ የተመረቁ ባለሙያዎችን በመቀበል ሀብት በመመደብና ስልጠናዎችን በመስጠት ወደ ስራ አስገብተናል። ይህንን ልምድም የማስፋት ስራው ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ተቋሙን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በማደራጀት አገልግሎቶቹ በቀላሉ ሕብረተሰቡ ጋር ተደራሽ እንዲሆኑ የሚሰሩ ስራዎችንም የማስፋት እቅድ ተይዟል። በተለይም በሕገወጥ መንገድ ዜጎችን ከቦታ ቦታ በማዘዋወር በኩል ያለውን ችግር ለመፍታት ጥቆማ መቀበያ ነጻ የስልክ መስመር የማዘጋጀት ስራ ተሰርተቷል፤ ይህም ከአይ ኦ ኤም ጋር የሚሰራ ሲሆን 6073 ነጻ የስልክ መስመር ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- ስነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ተክሴ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ዘመናዊ የቅንድብ አሰራር - «ኦምብሬ»

ሰሚራ በርሀ

የሴት ልጅ ውበት በብዙ መንገድ ይገለጻል፤ እንደየሰው ምርጫም ይለያያል፡፡ በሀገራችንም የሴት ልጅ ውበት በተለያየ መልኩ ይደነቃል፤ አንዳንዶች ምንም የማይወጣላት ውብ መሆኗን ሲገልጹ « ልቅም ያለች ቆንጆ» ይሏታል፡፡

ሴቶቹም የተፈጥሮ ውበታቸውን ለመጠበቅ፣ ይበልጥ ተውበውም ለመታየት የተለያዩ መዋቢያዎችን ሲጠቀሙ ይስተዋላል፡፡ ራሳቸውን ለማስዋብ ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች አንዱ ቅንድብን ማስዋብ ነው፡፡

ለእዚህም የተለያዩ የመዋቢያ መንገዶች ያሉ ሲሆን፣ ዘመናዊ የመዋቢያ ግብዓቶችን ተጠቅመው ራሳቸውን የሚያስውቡ ሴቶች ከሚጠቀሙባቸው ግብዓቶች አንዱ የቅንድብ ማስዋቢያ ነው፡፡ « ቡኒ ኩልን » አልያም ደግሞ ለእሱ ተብሎ የተዘጋጀ ዱቄት መሰል መዋቢያን በመጠቀም ቅንድባቸውን ያስውባሉ፡፡

ለወትሮው ቅንድብን ለማስዋብ አንደኛውና በብዙዎች ዘንድ የተለመደው አማራጭ « መቀንደብ» ወይንም የቅንድብን ቅርጽ ማስተካከል ነው፡፡ ይህ የቅንድብን ቅርጽ የማስተካከል ወይም የመቀንደብ ፋሽን ቅርጹ ከጊዜ ጊዜ እየተለያየ እና እየተሻሻለ ፋሽኑም እየተለወጠ ይገኛል፤ ቀጭን እና ወጥ ከሆነ የቅንድብ ቅርጽ የእንስቷን የቅንድብ ተፈጥሮ በመመልከት ያልበዛ ተፈጥሯዊ ቅርጹን የጠበቀ አቀነዳደብ የዚህ ወቅት ፋሽን ነው፡፡

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፣ ከምልከታ መረዳት እንደተቻለውም፤ እስከ አሁን ሲደረግ የቆየው በአብዛኛው የሌለን ውበት መጨመር፣ ማጉላት ነበር፤ አሁን ላይ ግን የመዋቢያ ግብዓቶችን ተጠቅመውም ቢሆን ተፈጥሯዊነቱን ያልለቀ አልያም ያልተጋነነ ሜክ አፕ መጠቀም ጊዜው የሚጠይቀው ፋሽን ሆኗል፡፡

ታዲያ እንስቶች ቅንድባቸውን በሚሰሩበት ወቅት በየእለቱ ግብዓትን በመጠቀም ማስዋብ ጊዜ የሚወስድ እና ችሎታንም የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ በተለያዩ የውበት ሳሎኖች ውስጥ የሜክአፕ ባለሙያዎች እንደሚገኙ ሁሉ፤ አሁን ላይ ደግሞ ቅንድብን በሒና የሚያስውቡ ባለሙያዎች መጥተዋል፡፡

የሒናው ዱቄት በሚያስፈልገው መልኩ ከተበጠበጠ በኋላ በእንስቷ ምርጫ እና የቅንድብ ቅርጽ ልክ ይቀባል፤ ብዙም ደቂቃ ሳይወስድ እንዲለቅም ይደረጋል፡፡ ከዚያም እንስቷ ለፈለገችው ፕሮግራም ቅንድቧን ለማሳመር መጨነቅ ሳይጠበቅባት ቅርጹን እንደያዘ የሚቀመጥ በመሆኑ እስከ አንድ ሳምንት ለሚዘልቅ ጊዜ ትጠቀምበታለች፡፡

አንድ የፈጠራ ሀሳብ ባለበት ብቻ አይቆምም፤ በየጊዜው እየተሻሻለ እና እየተለወጠ ይሄዳል። በመሆኑም እንስቶች ቅንድባቸውን ለማስዋብ የሚወስድባቸውን ረዘም ያለ ጊዜ ማስቀረት የሚችል ሀሳብ በብዙዎች ተቀባይነት አግኝቷል። ይህ ሀሳብ « ኦምብሬ ቅንድብ ታቱ » ይሰኛል። ይህም ንቅሳት ያልሆነ ነገር ግን ረዘም ላለ ጊዜ መጠቀም የሚችሉበት ቴክኖሎጂ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ከተሰሩት በኋላ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት ድረስ የሚቆይ በመሆኑም በሚሰራበት ወቅት እጅግ ጥንቃቄን ይጠይቃል፡፡ ለሚሰሩ ባለሙያዎችም ስልጠና ይሰጣል፡፡

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ወደ ኦምብሬ ቅንድብ ታቶ ባለሙያዎች የምትሄድ እንስት በቅድሚያ ከጤና አኳያ የሚቀርብላትን መጠይቅ ከሞላች በኋላ ለመሰራት ዝግጁ ትሆናለች። ከዚያም የመጀመሪያ ስራው የእንስቷን ፊት ማጽዳት ይሆናል፡፡ ፊቷ በአግባቡ ከተጸዳ በኋላ፣ እንደ እንስቷ የፊት ቅርጽ በባለሙያዋ ይለካል፡፡ ይህ የሚደረገው ሴቶች በተፈጥሮ ያላቸው ቅንድብ ቅርጽ የሚለያይ በመሆኑ ነው፡፡ የሚሰራው ደግሞ ልኬቱም ቀጠን ያለ ክርን በመጠቀም በቅንድቧ መጀመሪያ፣ መሀከልና፣ መጨረሻው ላይ ምልክት ይደረጋል። ባለሙያዋ ምልክት ባደረገችበት ቦታ ላይም በቅንድብ ማሳመሪያ ኩል ከተሰራ በኋላ ደንበኛዋ እንድትመለከተው ይደረጋል፤ በዚህም መውደዷን እና አለመውደዷን ትገልጻለች፤ አልያም ያላትን ሀሳብ ታካፍላለች፡፡

ኦምብሬ የቅንድብ ስራን ሰርቶ ለማጠናቀቅ ከሶስት እስከ አራት ሰዓት ይወስዳል፤ የሚሰራውም ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቀጭን መርፌ ነው። የቅንድብ ስራውን አንድ ጊዜ ከተሰሩ በኋላ ከአንድ ዓመት እስከ ሶስት ዓመት ይቆያል፤ ይሁን እንጂ ቆይታው እንደየ ሰው የቆዳ አይነት እና አቀባበል ይለያያል፤ ይህን ለመከታተልም እንደ አስፈላጊነቱ ወደተሰሩበት ሳሎን አልያም ባለሙያ መሄድ ይቻላል፡፡

ኦምብሬውን ለመስራት ባለሙያዎች የሚጠቀሟቸው የግብዓት ቀለሞች ከእጽዋት የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ እንስቷ ከእነዚህ ቀለሞች የምትፈልጋቸውን እንድትመርጥ ይደረጋል፤ ቅንድቧ ተሰርቶ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሕመም እንዳይሰማት ማደንዘዣ መርፌ ትወጋና ስራው ይጀመራል፡፡ ሰርቶ ለማጠናቀቅም ከሶስት እስከ አራት ሰዓት ይወስዳል፡፡

ቅንድቧን ተሰርታ ከጨረሰች በኋላም የተሰራችው ኦምብሬ ቦታውን እንዲይዝ እና እንዳይለቅ አልያም ደግሞ ቆዳዋ እንዳይቆጣ ወይንም ኢንፌክሽን እንዳይፈጥር ከሰባት እስከ 10 ቀን ውሀ እንዳይነካው ትመከራለች፡፡ ከዚያም የሚቀባ ውህድ ይሰጣታል፡፡

እንስቷ በምትሰራበት ወቅት ባለሙያዋ የምትጠቀመው መርፌ ቆዳዋ እንዲከፈት ስለሚያደርገው እንድትቀባው የሚሰጣትን ውህድ እና የምታደርገውን ጥንቃቄም ለመከታተል እንዲቻል እስከ ስድስት ሳምንት ባለው ጊዜ ከቆየች በኋላ ተመልሳ ወደ ባለሙያዋ ትሄዳለች፡፡ ከዚያም ቅንድቧ ተፈጥሯዊ የሆነ እይታ ይኖረዋል፤ ይህ አሰራር ከሚጨምረው ውበት ባሻገርም ሴቶች ቅንድባቸውን ለማስተካከል የሚያጠፉትን ጊዜን ይቆጥባል፡፡

ውበትን ለመጠበቅ በየጊዜው የሚተዋወቁ ቴክኖሎጂዎች ቢኖሩም እንስቶች መርሳት የሌለባቸው ጉዳይ በሚሰሩበት ቦታ እና በሚመርጡት ባለሙያ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም አንዲት ቅንድቧን ኦምብሬ የተሰራች እንስት ምንም እንኳን ቅንድቡ የሚሰራበት መንገድ ቀላል ቢሆንም በተገቢው መልኩ ካልተሰራ እና ጥንቃቄ ካልተደረገበት ለማስለቀቅ የሚደረገው ሙከራ የሚሰራበትን ያህል ቀላል አይሆንም፡፡

«ኦምብሬ ቅንድብ » አሰራር በሌሎች ሀገራትም በተለመደ መልኩ የሚሰራ ሲሆን፣ ሙያውን የሚያስተምሩ ባለሙያዎችም በብዛት ይገኛሉ፡፡ በሀገራችንም ይህ ሙያ ያላቸው እና አገልግሎት የሚሰጡ የውበት ሳሎኖች እና ባለሙያዎች ቢኖሩም የመማሪያ ስፍራዎች ግን እምብዛም አይደሉም፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የወላጆች አርአያነት እስከምን ድረስ?

እየሩስ ተስፋዬ

በአንድ አውቶብስ ውስጥ እያለሁ የተፈጠረ ክስተት ነው። እናት ልጇን አቅፋ የአውቶብሱ የመጀመሪያ ወንበር ላይ ተቀምጣለች። ልጇ እንቅልፉ መጥቷል። እያንቀላፋ በመሀል ብንን ብሎ ይነሳል። «ይኸውልህ ትተኛና አጋጭሃለሁ» እያለች ታስፈራራዋለች። በዚህ መሀል እንቅልፍ ሸለብ ሲያደርገው ተነሳ እያለች በመወዝወዝ ትቀሰቅሰዋለች። ይህን የምታደርገው ልጁ እንቅልፍ ከወሰደው ተሸክማው ለመሄድ እንዳይቸግራት አስባ ነው። ከቁጣ አልፋ ተሳፋሪውን የረበሸችውም ለዛ ነው።

እኔን ጨምሮ አውቶብሱ ውስጥ ያለን ተሳፋሪዎች ለእርሷ ባንነግራትም በድርጊቷ «ያማታል እንዴ?» የሚል መልስ የማንጠብቅበት ጥያቄ ከሁላችንም ፊት ይነበባል። በዚህ ሂደት «ልጇን ማባበል አትችልም ነበር? ወይም ልጇ ቀስ ብላ ማስረዳት አትችልም ነበር?» ሕፃን ነው! እንዲህ ነበር መቆጣት እና መጮህ ያለባት?» እያልኩ ተደራራቢ ጥያቄዎችን ለራሴ እንድጠይቅ አደርጎኛል። ብቻ የእናት እና ልጅ መጨረሻ ምን እንደሆነ ሳላውቅ ቀድሜ ከአውቶቡሱ ወረድኩ። ሌሎች መሰል እንዲህ አይነት የልጅ ስነ ልቦና ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ድርጊቶችን በየቦታው እየተለመዱ ነው።

አብዛኛው ልጅ የወላጆቹ፣ የቤተሰቡ፣ የማኅበረሰቡ እንዲሁም ከፍ ሲል የአገሪቱ ነጸብራቅ ነው። ቤት ውስጥ ያየውን፣ የተመለከተውን እና የተነገረውን ነገር ነው በውጭ የሚያንጸባርቀው። «ልጆች ነጭ ወረቀት ናቸው። » የሚባሉትም ለዚህ ነው። የሳልንባቸውን ሁሉ ፍንትው አድርገው መልሰው ያሳዩናል። በእነሱ ውስጥ ራሳችንን በሚገባ እናይበታለን። ትምህርት ቤታቸውም ይሁን ሌላ ቦታ መሄድ ሳይጠበቅብን ድርጊታቸውን በማየት ውሏቸው ምን እንደሚመስል የመገንዘብ ዕድላችንም ሰፊ ነው። ወደድንም ጠላንም ልጆች እንደ አርአያ የሚያዩት በቅርባቸው የሚመለከቱን ሰው ነው። ለዚህ እኮ ነው እንቅስቃሴያቸው ሁሉ በቅርብ እንደሚያዩት ሰው የሚሆነው። እንደ እነርሱ መሄድ ይፈልጋሉ። አለባበሳቸው፣ አነጋገራቸው እና አንደበታቸው ሁሉ የእነርሱ ቅጂት ይሆናል።

አልተጠናም እንጂ የውጭ አገራት ፊልሞች ተተርጉመው በየቴሌቪዥኑ መቅረብ ከጀመሩ ወዲህ አዋቂዎችን ጨምሮ ብዙ ወጣቶችና ታዳጊዎችን ባህሪ በብዙ መልኩ ተቀይሯል። ታዳጊዋ የሰፈራችን ልጅ ናት። በወቅቱ ዕድሜ ዘጠኝ ቢሆን ነው። እናቷ ትርጉም ፊልሞችን በቴሌቪዥን ማየት አትፈልግም። ሰው የቱንም ያህል ሊያማልላት ቢሞክርም ምርጫዋ አልነበረም። አንድ ቀን ልጅ እናንተን ፊልሞቹ ላይ ያሉ ገፀ ባህሪያትን እየጠራች እንዲህ ሆነ እንዲያ? እያለች ስትጠይቃት ግራ ገባት። ቤት ውስጥ ስለማትከፍት እንዴት እንዳወቀች ጠየቀቻት። ልጅቷም «እረ ባክሽ አንቺ ብትከለክይንም የትምህርት ቤት ጓደኞቻችን እኮ ይነግሩኛል። » ብላ መለሰችላት። ምናልባት ከዚህ ንግግር ብዙ ነገር መረዳት ይቻላል። ልጆቻቸውን በአግባቡ ለማሳደግ ወላጆች ቢጥሩም በትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ተጽዕኖ የቤተሰብ ድካም ከንቱ ሆኖ ይቀራል። በልጅነት አዕምሯቸው ማወቅና ማድረግ የማይገባቸውን ነገር እንዲያደርጉ ይገደዳሉ። አንዳንድ ወላጆች ለልጆቻቸው ምን ማስተማር እና ምን ማሳየት እንዳለባቸው ግንዛቤው እንደሌላቸውም ለመረዳት ቀላል ነው። ብቻ በአንዳንድ የቤተሰብ በኩል ግዴለሽነትን እንዳለ ይታያል።

ጭራሽ አሁን አሁንማ በማሕበራዊ ሚዲያ ላይ ልጆችን ይዞ በመውጣት ግማሹ ለማሳቅ ግማሹ ደግሞ ራሱ የሚያደርገውን ድርጊት ልጁ እንዲደግምለት ሲጥር እንመለከታለት። ይህ ትክክል አይደለም። ልጆች እንደልጅነታቸው ተጫውተው እና ቦርቀው ነው ማደግ የሚገባቸው። እንዲህ ያሉ ወላጆች አስበውበት አይመስልም ይህን የሚያደርጉት። ምናልባትም በስሜት ሌላው ስላደረገው ብቻ «ለምን እኔስ ይቅርብኝ? በሚል ፉክክር ይመስላል ድርጊቱን የሚፈፅሙት ።

አንዳንድ ቤተሰብ ደግሞ ልጅን ከመጠን በላይ በመቆጣጠር፣ ነፃነት በማሳጣት እና የቤተሰቡን ሃሳብ ብቻ የሚሰማ ልጅ ብቻ አድርገው ማሳደግ ትክክለኛ የልጅ አስተዳደግ የሚመስለው ወላጅ ቁጥር አናሳ የሚባል አይደለም። ከእንዲህ አይነቱ ቤተሰብ የወጡ አብዛኛዎቹ ልጆች ግን ፈሪ፣ በራሳቸው የማይተማመኑ፣ ጭምት፣ ከሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት የተገደበ ሊሆን እንደሚችል ምንም ጥያቄ የለውም። አፈንግጦ የወጡ ቀን ደግሞ ማንንም የማይሰሙ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመት የማይችሉ ወላጆች መኖራቸውን በማሰብ ነው ልጆች ላይ ከሚሠራው ሥራ ባልተናነሰ ወላጆች ላይ መሠራት አለበት የሚባለው።

«ነገርን ነገር ያነሳዋል» አይደል የሚባለው፤ የዛሬው ትዝብት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተመለከትኩትን ነገር አስታወሰኝ። አንዲት ሴት ጧፍ እያበራች ነበር። በግምት ዕድሜው ከስምንት እስከ አስር ዓመት የሚሆን ልጅ አብሯት አለ። ጧፉ በርቶ ሳያልቅ ተቀበላትና አጠፋው። ከሴትየዋ ምንም አይነት ምላሽ አልተመለከትኩም። ቀጥሎ እየጠፋ ባለው ጧፍ እጇን ለማቃጠል ሲሞክር «ተው!» ብላ ዝም አለች። በተደጋጋሚ ለማቃጠል ሲሞክር፤ ሌሎች ሰዎች ነበሩ «እረፍ እንዲህ ይደረጋል እንዴ?» ብለው የተቆጡት። እርሷ ዝምታን የመረጠችው። ካላችበት ቦታ አንጻር ሌሎችን ላለመረበሽ ይሆናል ዝምታን የመረጠችው። ነገር ግን እንዲህ ያለው ቸልተኝነት ከተደጋገመ ነገ እናቱን የሚጠር ሳይሆን የሚደበድብ ልጅ እንዲፈጠር መፍቀድ ነው። ሲቀጥል ይህን ልማድ ለማዳበር የቻለው ከቤት ውስጥ የነበረው አያያዝ ምን አልባትም ጥሩ ባለመሆኑና በቁንጥጫ ያላደገ ሊሆን ይችላል።

ሁሉም እንደሚያስታውሰው ከጥቂት ዓመታት በፊት ልጆች የኅብረተሰቡ ነበሩ ለማለት ያስደፍራል። ጎረቤት የራሱ ያልሆነ ልጅ ሲያጠፋ ይገስጻዋል፣ ይቆጣዋል፤ ይቀጣዋልም። ዛሬ እንዲህ ያለው ነገር አለ ለማለት ያስቸግራል። ብዙዎች «ምን አገባኝን?» ይመርጣሉ። ቢቀጣ ደግሞ «በእኔ ልጅ ምን አገባህ? » ሊባል እንደሚችል ያምናልና ። በግዴለሽነት ነገሩን ለማለፍ ይገደዳል።

ሌላው ልጆች መጽሐፍትን ገዝተው እንዲያነቡ፣ አንብበው ከጨረሱ በኋላም ምን እንደተማሩ ከመጠየቅ ይልቅ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ታብሌት እና መሰል የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመግዛት ሳያውቁት ልጆቻቸው ግለኝነትን እንዲለማመዱና የ«ጌም» ሱሰኛ እና የመሳሱትን ችግሮች በልጆቻቸው ላይ እንዲፈጠር የሚያደርጉ ወላጆችን መኖራቸውን እየታዘብን ነው።

በአገራችን ከልጅ ጋር የተያያዙ አባባሎች ብዙ ናቸው። «ልጅ እና ጫማ ወደ አልጋ»፣ «ልጅ ያቦካው ለእራት አይበቃም» ፣«ከልጅ አትጫወት ይወጋሃል በእንጨት» እና መሰል አባባሎችን መጥቀስ ይቻላል። አሁን ላይ ደግሞ «ሁሉም ነገር ለልጆች» የሚል ይመስላል አባባሉ። እንዲህ ጫፍ እና ጫፍ ያለውን አስተሳሰብ ማመጣጠን እንዲሁም ሚዛናዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ ግን "ዘመኑን የተረዳ፣ እንዴት ይሁን? ቀጥሎስ ምን ላድርግ? የማደርገው ነገር ልጆቼን ይጎዳል ወይስ ይጠቅማል? ከእኔስ ምን ይማራሉ?" ብሎ የሚጠይቅና በብዙ መልኩ አርአያ የሚሆን ወላጅ መኖር አለበት። ታዲያ ልጆች በሥነ ምግባር የታነጹ እንዲሆኑ ከሚሠራው ሥራ እኩል በእኩል ወላጆች ላይ መሥራት ግድ የሚልበት ወቅት ላይ የምንገኝ አይመስላችሁም?